ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 242 ግንቦት 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# "ኢትዮጵያን በተሻለ ፍጥነት ስማሳደግ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የግድ መጠቀም አለብን"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን በተሻለ ፍጥነት ማሳደግ ካስፈለገ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የግድ መጠቀም አለብን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚሊኒየም አዳራሽ የተሰናዳውን የ2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ ትናንት ከፍተዋል።

ኤክስፖውን ከጎበኙ በኋላ እንደተናገሩት፤ ጥራትና ውበት ያላቸውን የሀገር ውስጥ ምርቶችን በሰፊው

"ኢትዮጵያን በተሻለ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

# ኢትዮጵያ
## ኢኮኖሚዋን የሚሸከም ከአንድ በላይ ወደብ ያስፈልጋታል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን የሚሸከም ከአንድ በላይ ወደብ የግድ ያስፈልጋታል ሲሉ የኢትዮጵያ ሶሻል ፓርቲ ሊቀመንበር በየነ ጴጥሮስ (ፕ/ር) ተናገሩ።

ሊቀመንበሩ ከኢፕድ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ በጂቡቲ ወደብ ብቻ በሚገኘው አገልግሎት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ማርካት አይቻልም። ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን የሚሸከም ከአንድ በላይ ወደብ የግድ ያስፈልጋታል።

በእጅ የተያዘ ምንም ነገር በሌለበት ሁኔታ በቀጣይ በርከት ያለ የባሕር በር መጠቀም የግድ ይላል ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ እንደ ኢትዮጵያ ያለ የባሕር በር የሌለው ሰፊ ሕዝብ የያዘ ሀገር ወደ ባሕር የሚገባባቸውንና የሚወጣባቸውን በሮች ማስፋት ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።

አንዱ ወደብ ላይ ችግር የሚፈጠር ከሆነ ወደሌላ አማራጭ መሄድና መጠቀም ይችላል ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ምክንያቱም የዛሬ ወዳጅ ነገ ባልተጠበቀ ጊዜ ሊቀየር ስለሚችል "ይህ

ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ በመጀመሩ
## የፋይናንስ ዘርፉ መሠረታዊ ሽግግር እያደረገ ነው
### - የምሥራቅ አፍሪካ የፋይናንስ ጉባዔ መካሄድ ጀምሯል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ በመጀመሩ የፋይናንስ ዘርፍ በመሠረታዊነት እየተሸጋገረ ነው ሲሉ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ገለጹ። ሰባተኛው የምሥራቅ አፍሪካ የፋይናንስ ጉባዔ ትናንት በአዲስ አበባ መካሄድ ጀምሯል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ በጉባዔው እንደገለጹት፤ የካፒታል ገበያ በመጀመሩ የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ በመሠረታዊነት እየተሸጋገረ ነው።

ብሔራዊ ባንክ አዲስ ስትራቴጂ ዕቅድ ማውጣቱንም አቶ ማሞ ገልጸዋል።

የካፒታል ገበያው የኢትዮጵያ ኩባንያዎችን አክሲዮን ዕዳ ለማገበያየት፣ ደህንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ መድረክ እንደሚፈጥር ጠቅሰው፤ የህብረተሰቡን ቁጠባ ለማሰባሰብና ለመመደብ አማራጭ መንገዶችን እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

የፋይናንስ ዘርፉ በተደራሽነት፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂዎችና በዘመናዊ የአያያዝ ሥርዓቶች አጠቃቀም ረገድ ከፍተኛ እድገት ማሳየቱን ጠቅሰው፤ በተለይም



ፎቶ፡ ሃይለ አብርሃ

አቶ ማሞ ምህረቱ

የሞባይል ባንክ፣ የሞባይል ቦርሳ፣ የኢንተርኔት ባንክ፣ ኤቲኤም፣ አዳዲስ ዲጂታል ቁጠባዎችና የብድር እቅዶች መደበኛ እየሆኑ መምጣታቸውን አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ የካፒታል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የተጣለው የቪዛ ገደብ
## የኢትዮጵያና የኅብረቱን ታሪካዊ ግንኙነት የማይመጥን ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ላይ የተጣለው የቪዛ ገደብ የኢትዮጵያና የአውሮፓ ኅብረትን ታሪካዊ ግንኙነት የማይመጥንና ጊዜውን ያልጠበቀ ውሳኔ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች የፕሬስ ነፃነትን አስመልክቶ የሚያወጧቸው የደቦ መግለጫዎች ኢትዮጵያ እንደማትቀበልም ተገልጿል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓ ኅብረት በኢትዮጵያ ላይ የጣለውን የቪዛ ገደብ፣ ተቀማጭነታቸውን አዲስ አበባ ያደረጉ የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች እያወጡ ያሉትን መግለጫና አበይት ሳምንታዊ የዲፕሎማሲ ሁነቶችን አስመልክቶ ትናንት መግለጫ ሰጥቷል።

መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ነብዩ ተድላ እንደገለጹት፤ መንግሥት በሕገወጥ መንገድ በአውሮፓ የሚኖሩ ዜጎችን ለመመለስ እየሠራ ባለበት ወቅት የአውሮፓ ኅብረት ፈጣን ምላሽ አልሰጠም በሚል የጣለው የቪዛ ገደብ የኢትዮጵያና የኅብረቱን

የተጣለው የቪዛ ገደብ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አቶ ነብዩ ተድላ




# “ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ብቸኛው አማራጭ ነው”

- ምሁራን

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ብቸኛው አማራጭ ነው ሲሉ ምሁራን ገለጹ። በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ጠንካራ አደረጃጀትና የዲሞክራሲ ሥርዓት መሠረት ያደረጉ ባለመሆናቸው ዘላቂ ውጤት ማምጣት እንደተሳናቸው ሙሁራኑ ጨምረው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አብዮት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትሩፋቶችን የተሻገሩ እዳዎች በሚል ርዕስ 4ኛው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ሴሚናር ትናንት ተካሂዷል።

ሴሚናሩ የኢትዮጵያ አብዮት ከ50 ዓመት በኋላ፤ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ትሩፋቶችና የተሻገሩ ዕዳዎች በሚል ርዕስ ነው የተካሄደው።

የፖለቲካ ምሁር አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር) በውይይቱ ወቅት እንደገለጹት፤ በተለያዩ ዘርፎች ስርነቀል ለውጥ ማምጣት የሚቻለው ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ሲቻል ነው።

ሰላማዊ ትግል ማዳበር ዋነኛው ችግር ለመፍታት ወሳኝ ነው ያሉት ዶክተር አረጋዊ፤ ለፖለቲካዊ መፍትሔም እውቀትንና የዴሞክራሲ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ ውይይት ማሳደግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ በተደረጉ የለውጥ እንቅስቃሴዎች አብዮተኞች ለውጥ ቢፈልጉም በምን ሁኔታና በየትኛው ዘዴ እንዲሁም ምንን ማስቀደም እንዳለባቸው ባለማወቃቸው ተጨባጭ ለውጥ ሳያመጡ ተበታትነው ቀርተዋል ሲሉም አብራርተዋል።

ጠንካራ አደረጃጀትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ባለማዳበራቸው የውስጥ ልዩነቶቻቸውን እንኳን በንግግር



አረጋዊ በርሄ(ዶ/ር)



ባህሩ ዘውዴ(ፕ/ር)

መፍታት ተስኗቸው እንደነበር አስታውሰዋል።

እንደ ዶክተር አረጋዊ ገለጻ፤ ለውጥ ውጤታማና ዘላቂ ሊባል የሚችለው ደም ሳይፈስ ንብረት ሳይጎዳና ሀገራዊ እድገት ሳይገታ በሰላማዊ መንገድ ሲሆን ነው።

የታሪክ ተመራማሪና ሙሁር ባህሩ ዘውዴ (ፕ/ር) በበኩላቸው፤ የሚፈለገው ሀገራዊ ለውጥ ለማምጣት በመጀመሪያ የዲሞክራሲ ባህል ማጎልበትና እስካሁን ካለው የፖለቲካ አዙሪት መውጣት ያስፈልጋል ብለዋል።

የ1966 እና የ1983 የአብዮቱ ጥያቄዎች አግባብነት ቢኖራቸውም ተጨባጭ ውጤት ሊያስገኙ አልቻሉም ያሉት ፕሮፌሰር ባህሩ፤ ሁለቱም የፖለቲካና የዘር ፍጅት አስከትለዋል ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ገለጻ፤ በተለይ የ1983 ዓ.ም አብዮት ከጥቅም ይልቅ በብሔር መከፋፈልን ወልዷል።

በተጨማሪም በሁለቱም አብዮቶች የዲሞክራሲ ባህል ባለመዳበሩ አብዮተኞቹ እርስ በእርሳቸው እንኳን መቻቻልና መነጋገር የማይቻልበት ሁኔታ እንደነበር አስታውሰዋል።

በኢትዮጵያ ባለፉት ጊዜያት ከነበረው ትክክለኛ ያልሆነ የለውጥ እንቅስቃሴ በተጨማሪ መሪዎች ምሁራኑ የሚያቀርቡትን የመፍትሔ ሃሳብ አለመቀበል ሌላኛው ትልቅ ፈተና እንደነበርም ነው ፕሮፌሰር ባህሩ ያብራሩት።

የአሁኑ ትውልድ ካለፈው በመማር አስቀድሞ በራሱ ላይ ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል ያሉት ደግሞ አምባሳደር ታደለች ኃይለሚካኤል ናቸው።

በሀገሪቱ አብዮት ካስፈለገም ድህነት ላይ መዝመት ይገባዋል ያሉት አምባሳደር ታደለች፤ መፈራረጅን በመተው ሀገሪቱ ወደ ፊት በምን ዓይነት ለውጥ ላይ መድረስ አለባት የሚለው ላይ መነጋገር አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል።

በሴሚናሩ በተለያዩ ርዕሶች ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።



አቶ ታገሰ ጫፎ

# የኮንስትራክሽን

## ኢንዱስትሪው ባሉበት ተግዳሮቶች የሚባክነውን የሀገር ሀብት ለማዳን መረባረብ ያስፈልጋል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ ባሉበት ተግዳሮቶች ምክንያት የሚባክነውን የሀገር ሀብት ለማዳን መረባረብ ያስፈልጋል ሲሉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ ገለጹ፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተግዳሮቶች መውጫ መንገዶች እና የሕግ አውጪው ሚና በሚል ርዕስ በትናንትናው ዕለት የፓናል ውይይት አካሂዷል፡፡

በፓናል ውይይቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ እንደገለጹት፤ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ በርካታ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍና ብዙ የሀገሪቱን ሀብት የሚጠቅም ነው፡፡

ይሁን እንጂ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ በተለያዩ ተግዳሮቶች እየተፈተነ መሆኑን አንስተው፤ በዚህም በዘርፉ የሀገሪቱ ሀብት የሚባክንበትም ነው ሲሉ ገልጸዋል ፡፡

አፈጉባኤው፤ ዘርፉ ለሀገር የሚያበረክተውን አወንታዊ አስተዋጽኦ በመገንዘብ ያሉትን ተግዳሮቶች ለመፍታት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊረባረብ ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ አፈጉባኤው ገለጻ፤ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍና ዘርፉን ለማዘመን መንግሥት የተለያዩ እቅዶችን አውጥቶ እየሠራ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም የግሉ ዘርፍ እና የዘርፉ ባለሙያዎች ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፉ የመንግሥት ከ60 እስከ 65 በመቶ የሚሆነውን የካፒታል በጀት የሚጠቀም መሆኑን ገልጸው፤ በርካታ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ለማምጣት፣ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር፣ ሌሎች ዘርፎች እንዲስፋፉ ለማድረግ እንዲሁም ለሀገር ዕድገት ወሳኝ ሚና የሚጫወት ትልቅ ዘርፍ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

መንግሥት ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያበረክተውን ሚና በመረዳት ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረጉ ከሪፎርሙ በኋላ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ማየት ተችሏል ብለዋል፡፡

በመድረኩ የዘርፉ ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑና መፍትሔዎቻቸውን የሚያመላክቱ ጥናታዊ ጽሁፎች በምሁራን ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን፤ በጥናቶቹም በዘርፉ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች በአንድ አካል ተፈጥረው በአንድ አካል መፍትሔ የሚያገኙ አለመሆናቸው ተመላክቷል፡፡

በተጨማሪም በጥናቶቹ ዋነኞቹ የዘርፉ ተግዳሮቶች የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የግብዓት እጥረት፣ የግዢ ሥርዓት አለመዘመን እንዲሁም የዋጋ መናር እና የጸጥታ ችግር እንደሆኑ ተነስቷል፡፡

ወጥ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መመሪያ መዘርጋት፣ የግዢ ሥርዓቱን ማዘመን እንዲሁም በዘርፉ በቂ የተማረ የሰው ኃይል እንዲኖር ማስቻል የሚሉ የመፍትሔ ሃሳቦችም ተቀምጠዋል፡፡



# ጨንቻን ከሁለት የዞን ከተሞች ጋር የሚያገናኘው የአስፋልት መንገድ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

**ዜና ሀተታ**

“ፈጣሪ ይመስገን የማህበረሰቡ የዘመናት የመንገድ መሰረተ ልማት ጥያቄ አሁን ላይ ምላሽ አግኝቷል” ይላሉ የጨንቻ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ ተረፈች አሸናፊ። በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ ዞን የምትገኘው ጨንቻ የጋሞ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት ዋና መቀመጫ ሆና አገልግላለች። ሆኖም ከተማዋን ከሌሎች የዞን ከተሞች ጋር የሚያገናኝ መንገድ አልነበራትም።

የሞርካ - ግርጫ - ጨንቻ መንገድ ግንባታ የጨንቻ ከተማን ከሌሎች ሁለት የዞን ከተሞች ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ ይህም የከተማዋን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያፋጥናል የሚሉት ወይዘሮ ተረፈች፤ መንገዱ ታካሚን በተሻለ ፍጥነት ጤና ተቋም ለማድረስ እና አምራች ምርቱን ለማዕከላዊ ገበያ እንዲያቀርብ ያደርጋል ባይ ናቸው።

የባጃጅ፣ የጭነት እና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ወደ ጨንቻ ከተማ ለመግባትም ሆነ ከከተማው ለመውጣት ሲቸገሩ መቆየታቸውን ወይዘሮ ተረፈች ያስረዳሉ፡፡ በከተማዋ የግብርና ምርቶችና የተለያዩ ማዕድናት በብዛት ቢኖርም በመንገድ ችግር ምክንያት ለገበያ ማቅረብ እንዳልተቻለ ይናገራሉ።

በጨንቻ ከተማ የአስፋልት መንገድ ባለመኖሩ ለትራንስፖርት አገልግሎት እጦት፣ ለተጨማሪ ወጪ እንዲሁም ህሙማንና ወላድ እናቶችን ወደ ህክምና ተቋማት ለማድረስ ለዓመታት ሲቸገሩ መቆየታቸውንም ወይዘሮ ተረፈች በማሳያነት ያነሳሉ፡፡ “ከተማዋን ከሌሎች ከተማዎች ጋር የሚያገናኝ መንገድ እንዲሠራ በተደጋጋሚ በአካልና በደብዳቤ ስንጠይቅ ቆይተናል” ነው ያሉት።

“አሁን ላይ ጥያቄያችን ምላሽ አግኝቶ የመንገዱ ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል” የሚሉት ወይዘሮ ተረፈች፤ የመንገዱ ግንባታ ሲጠናቀቅ ለአካባቢው ማህበረሰብ የገቢ ምንጭ እንዲሁም ለከተማዋ ዕድገት መሠረት እንደሚሆን ያምናሉ።

የጨንቻ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ደመላሽ ንጉሴ በበኩላቸው፤ ጨንቻ ከተማ የ127 ዓመት ዕድሜ ቢኖራትም ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች፣ የአስፋልት መንገድ እና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች አለመኖር ብዙ እንቅስቃሴ የማይታይባት ከተማ አድርጓት መቆየቱን ነው የተናገሩት።

“የከተማዋ ትልቁና ዋነኛው ችግር የመንገድ መሠረተ ልማት ነው” የሚሉት አቶ ደመላሽ፤ “መንገድ የሌለው ከተማ በጋን ውስጥ እንዳለ መብራት ብንቆጥረው ማጋነን አይሆንም” ባይ ናቸው።

እየተገነባ የሚገኘው መንገድ ሞርካ፣ ግርጫ እና ጨንቻ የተባሉ ሶስት የዞን ከተሞችን የሚያገናኝ ሲሆን፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለመጓጓዝ ይወስድ የነበረውን የጉዞ ጊዜ በሁለት ሰዓት ተኩል ይቀንሳል ነው ያሉት።

የመንገድ መሠረተ ልማት በከተማዋ እንዲኖር የአካባቢው ማህበረሰብ ለአርባ ዓመታት ለመንግሥት ጥያቄ ሲቀርብ መቆየቱንም ገልጸዋል።

መንገዱ እየተሠራ በመሆኑና የመንገዱ አለመሠራት ከዚህ በፊት ያስከትል የነበረውን ችግር በመቅረፉ የተሰማቸውንም ደስታ የገለጹት ደግሞ በጨንቻ ከተማ ለአራት ዓመታት የትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩት ሹፌር ደመላሽ አድማሱ ናቸው።

“የመንገዱ ግንባታ በተሽከርካሪዎች፣ በከተማዋ ዕድገት፣ በማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚቀርፍ በመሆኑ እርካታ ተሰምቶኛል” የሚሉት ሹፌር ደመላሽ፤ በተለይ በመንገዱ አስቸጋሪነት ምክንያት ለተደጋጋሚ ብልሽት የሚዳረጉት ተሽከርካሪዎች ማሰሪያ የሚያወጡትን ወጪ የሚቀንስላቸው በመሆኑ ተደስተዋል።


በጨንቻ ከተማ የአስፋልት መንገድ ባለመኖሩ ለማሽከርከር እንቅፋት ከመሆኑ ባለፈ በተሽከርካሪ አካል ላይ ጉዳት በማድረሱ በኅብረተሰቡና በአሽከርካሪዎች ቅሬታዎችን ሲያስነሳ መቆየቱንም ይገልጻሉ፡፡

የሞርካ - ግርጫ - ጨንቻ የመንገድ ግንባታ ካለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር የሚመለከተው አካል ፕሮጀክቱን በፍጥነት እንዲያጠናቅቅም ጠይቀዋል።

የሞርካ - ግርጫ - ጨንቻ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተጠሪ ኢንጂነር አስቻለው ባልቻ በበኩላቸው፤ መንገዱ ከዚህ ቀደም በጥርጊያ ደረጃ ላይ የነበረ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት እየተሠራ የሚገኘው አስፋልት ኮንክሪት ግንባታ ነው። በአሁኑ ወቅት መንገዱ 52 ነጥብ ሶስት ኪሎ ሜትር የደረሰ ሲሆን፤ ይህም የግንባታው አፈጻጸም 72 ከመቶ ደርሷል ነው ያሉት።

የመንገዱ ስፋት በወረዳ ከተማዎች 21 ነጥብ አምስት ሜትር፣ በቀበሌ ከተማዎች 12 ሜትር፣ በገጠር ስምንት ሜትር ስፋት አለው ያሉት ኢንጂነር አስቻለው፤ ሁሉንም የድልድይ ሥራዎች በማጠናቀቅ 39 ነጥብ አራት ኪሎ ሜትር የአስፋልት ንጣፍ ሥራ ተሠርቷል ሲሉ ገልጸዋል።

ፕሮጀክቱ የተጀመረው 2012 ዓ.ም ሲሆን፤ ከወሰን ማስከበር ክፍያ መዘግየት ጋር በተያያዘ የመንገድ ግንባታው መዘግየቱን ገልጸው፤ በውሉ መሠረት የፕሮጀክቱን ግማሽ ክፍል በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለማስረከብ እንዲሁም ቀሪውን በ2017 ዓ.ም ለማስረከብ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።



# በውሃ አቅርቦት

## እጥረት መቸገራቸውን በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የሣርቤት አካባቢ ነዋሪዎች ገለጹ

### - ቅርንጫፉ በአጭር ቀናት ውስጥ ችግሩ ይፈታል ብሏል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ምክንያት ለጤና፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እየተዳረጉ መሆኑን የአዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የሣርቤት አካባቢ ነዋሪዎች አስታውቀዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የመካኒሳ ቅርንጫፍ በበኩሉ፤ የአካባቢው ነዋሪዎች በአጭር ቀናት ውስጥ ውሃ አቅርቦት እንዲያገኙ ይደረጋል ብሏል።

በአዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ ሳርቤት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ማርታ ባየታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአካባቢው ላይ ውሃ ከጠፋ አንድ ወር አልፎታል። ይህም ለተለያዩ ወጪዎችና ችግሮች ዳርጓቸዋል።

ከዚህ ቀደም ውሃ ለአንድ ወር ያክል ጠፍቶ ቆይቶ አንድ ቀን ሌሊት ላይ የመጣ ቢሆንም በሰዓቱ ለተወሰነ ሰው እንደተዳረሰ እና መልሶ ከጠፋ አሁንም አንድ ወር ማስቆጠሩን አብራርተዋል።

በውሃ እጥረት ምክንያትም አንድ ጀሪካን ውሃን በ30 ብር ገዝቶ ለመጠቀም ግድ ሆኖብናል ያሉት ወይዘሮዋ፤ ይህም ከፍተኛ ወጪ ባለው ነባራዊ የኑሮ ውድነት ላይ ለተጨማሪ ተጽእኖ እና እንግልት እንደዳረጋቸው ተናግረዋል።

ችግሩን በተደጋጋሚ ለሚመለከተው አካል ያሳወቁ መሆኑን ወይዘሮ ማርታ ተናግረው፤ መስመር ተሰብሯል እና ውሃውን ከፍተናል የሚል እና የውሃ እጥረት አለ የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው ገልጸዋል።

እንዲሁም ውሃ ስለማይመጣ ተብሎ በቦቴ ውሃ ተልኮ የነበረ ቢሆንም፤ ውሃው ንጹህ ካለመሆኑ በተጨማሪ ለአካባቢው ማህበረሰብ ለማዳረስ በቂ ባለመሆኑ ከፍተኛ የሰዎች ትርምስ ያስከተለ እንደነበር ተናግረዋል።

ሌላዋ የአካባቢው ነዋሪ ወይዘሮ ኮከቤ ሀይሌ በበኩላቸው፤ በ20 ቀናት ውስጥ ምንም የውሃ አቅርቦት እንዳላገኙ ይናገራሉ።

በአካባቢው ላይ ውሃ ከ15 እስከ 20 ቀናት አለመኖር እየተለመደ የመጣ መሆኑን አስታውቀው፤ በንጹህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት አለመኖር ለንጽህና ጉድለት እና ለበሽታ እየተዳረጉ መሆኑን ይገልጻሉ።

በአካባቢው ላይ አረጋዊያን፣ ሕፃናት እና ታማሚ ይገኛሉ ያሉት ወይዘሮዋ፤ የችግሩን አስከፊነት በመረዳት የሚመለከተው አካል መፍትሔ ይስጠን ሲሉ ተናግረዋል።

የንጹሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ችግር በመኖሩ ውሃን ከተለያዩ ቦታዎች ለመግዛት ለሚወጣ ወጪ ብሎም እንግልት በአጠቃላይ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዳርጎናል፤ አስቸኳይ መፍትሔ ሊሰጠን ይገባል ያሉት ደግሞ የሣርቤት አካባቢ ነዋሪዋ ወይዘሮ አስራት ለገሰ ናቸው።

በአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የመካኒሳ ቅርንጫፍ የውሃ ስርጭት ቴክኒሺያን አቶ መኩሪያ ሙላቱ ለኢፕድ በሰጡት ምላሽ በተጠቀሱት አካባቢዎች የውሃ አቅርቦት ችግር መኖሩን አምነዋል።

የአቅርቦት ችግሩ በዋነኝነት መንስኤው የመብራት መቆራረጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህም የውሀ አቅርቦትን ተደራሽ ማድረግ እንዳልተቻለ አስታውቀዋል።

በተለይም በቂ የውሃ ኃይል በማይኖርበት ወቅት ዳገታማ አካባቢዎች ላይ በብዛት ውሃ አያገኙም ያሉት ኃላፊው፤ በመሆኑም ይህንን በመፍታት በትኩረት ሲሰራ የቆየ ሲሆን፤ በአጭር ቀናት ውስጥ ውሃ አቅርቦት እንደሚያገኙ አስታውቀዋል።

በዚህም ውሃ ከጠፋ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረና ያልተዳረሱ አካባቢዎችን በማጠራት ቅድሚያ እንዲዳረሱ በማድረግ ለሁሉም አካባቢ ተደራሽ እንዲሆን ይሠራል ብለዋል።

ይህንንም የውሃ አቅርቦት እጥረት ለማካካስ በቦቲ በማቅረብ የተወሰነ ተደራሽ መደረጉን ጠቁመው፤ ተመሳሳይ የአቅርቦት ችግር እንዳያጋጥም መብራት በማይኖርበት ወቅት የማካካሻ ውሃ ማግኘት የሚቻልበትን መንገድ የማመቻቸት ሥራን ከሚመለከታቸው ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

# የኢትዮ - አሜሪካ የዲፕሎማሲ ግንኙነትን

## የሚዳስስ የፎቶ ኤግዚቢሽን እየተካሄደ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮ - አሜሪካ የ120ኛ ዓመት የሁለትዮሽ ግንኙነትን ምክንያት በማድረግ የሁለቱን ሀገራት የዲፕሎማሲ ጉዞ የሚያሳይ የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን ተከፍቷል።

ኤግዚቢሽኑ ከሚያዚያ 30 እስከ ግንቦት 18 ቀን 2016 ዓ.ም የሚቆይ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ1903 በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስካሁን ያለው የሁለቱን ሀገሮች የሁለትዮሽ ግንኙነት ጉዞ የሚያሳይ ነው።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በኤግዚቢሽኑ መክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያና የአሜሪካ የሁለትዮሽ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት የተጀመረው በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እ.ኤ.አ ከ1903 ነው። በዚያን ጊዜ በዳግማዊ አጼ ምኒልክና በአሜሪካው ተወካይ ሮበርት እስኪነር መካከል የንግድ ስምምነት ተፈርሟል።

ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ ሀገራት መካከል ከአሜሪካ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያላት ሀገር ናት ያሉት አቶ ስለሺ፤ ሁለቱ ሀገራት በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በፀጥታና ደህንነት፣ በጤና፣ በትምህርት እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች በትብብር እየሰሩ ይገኛሉ ብለዋል።

እንደ አቶ ስለሺ ገለጻ፤ ሀገራቱ የሕዝብ ለሕዝብ እና የባህል ግንኙነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። በአሜሪካ የሚኖሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው የኢትዮጵያ ዲያስፖራዎች ለዚህ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።



አቶ ስለሺ እንዳሉት፤ ለእይታ የቀረበው የፎቶ-ግራፍ ኤግዚቢሽን በሀገራቱ መካከል የነበረው የቆየ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የሚያሳይ ነው።

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኤርቪን ማሲንጋ በበኩላቸው፤ ሁለቱ ሀገራት ለረጅም ጊዜ በቆየ የዲፕሎማቲክ ግንኙነታቸው በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና እንዲሁም በኢኮኖሚ እድገት በጋራ መራታቸውን የፎቶ ኤግዚቢሽኑ ያሳያል ብለዋል።

ኤግዚቢሽኑ የሁለቱ ሀገራት የቆየ ግንኙነት መረጃ በመስጠት በቀጣይ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ የፎቶ ኤግዚቢሽኑ የተዘጋጀው የሁለቱ ሀገራት የ120 ዓመታት የዲፕሎማቲክ ጉዞ በዓል ምክንያት በማድረግ መሆኑን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኤርቪን ማሲንጋ፣ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ፣ የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው እንዲሁም ሌሎች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የኤምባሲው ሠራተኞች በኤግዚቢሽኑ መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝተዋል።




# በኢትዮጵያ የሚገነባው የምስጢራዊ ህትመቶች

## ፋብሪካ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ያጠናክራል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሚገነባው ምስጢራዊ ህትመት ፋብሪካ ኢትዮጵያን በምስጢራዊ ህትመት ከአፍሪካ ቀዳሚ የሚያደርግና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የሚያጠናክር መሆኑን የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ ገለጹ።

በ55 ሚሊዮን ዶላር ወጪ የሚገነባው ምስጢራዊ ህትመት ፋብሪካ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ ከትናንት በስቲያ ተቀምጧል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የምስጢራዊ ህትመት ፋብሪካው ኢንቨስትመንት ብቻ ሳይሆን ወደ ዲጂታላይዜሽን የሚደረገውን ጉዞ ያረጋግጣል። ይህም ኢትዮጵያን በምስጢራዊ ህትመት ከአፍሪካ ቀዳሚ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ያጠናክራል።

በኢትዮጵያ እያደገ ለመጣው የህትመት፣ የፓኬጂንግና የዲጂታል አሠራሮች ተግባራዊነት ዕድገት የፋብሪካው መገንባት ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውና ሚስጥራዊ የደህንነት ማረጋገጫ ያላቸው ሰነዶች ህትመት በኢትዮጵያ ማምረት መቻል እንደሀገር ብቻ ሳይሆን እንደ አህጉር የሚታዩ ክፍተቶችን እንደሚሞላ ገልጸዋል።

ፋብሪካው የጃፓንና የኢትዮጵያውያን አጋሮች የመሠረቱት ቶፓን ግራቪቲ በተሰኘ ኩባንያ የሚገነባ መሆኑንም ተናግረዋል።

በቀጣዮቹ ጥቂት ወራትም ከዓለም አቀፉ የሲቪል አቪየሽን ፕሮቶኮል ጋር በተጣጣመ መልኩ ማይክሮ ቺፕ ያለውን ፓስፖርት በሀገር ውስጥ በማምረት ተደራሽ የማድረግ ሥራ እንደሚከወን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በኢኮኖሚው ዘርፍ እያስመዘገበች ያለችውን ዕድገት ለማፋጠን እና ሀገራዊ ዲጂታላይዜሽን በአጭር ጊዜ እውን ለማድረግ መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማስፋፋት እንደሚገባ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሀገሪቱን በተለያዩ ዘርፎች ወደ ፊት የሚያራምዱ ውጤታማ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑንም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ሺባታ ሂሮኖሪ በበኩላቸው፤ ቶፓን ግራቪቲ 120 ዓመት ያስቆጠረ አንጋፋ የሕትመት ድርጅት መሆኑን ጠቅሰው፤ በ137 ሀገራትም በምስጢራዊ ሕትመት ዘርፍ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠለት የህትመት ፋብሪካም በአፍሪካ የመጀመሪያ መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያና ጃፓን በተለያዩ መስኮች ጠንካራ ግንኙነት እንዳላቸው ገልጸው፤ ይህ ግንኙነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

ፋብሪካው በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየውን የፓስፖርት እጥረት ለመቅረፍ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው የገለጹት ደግሞ የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሰላማዊት ዳዊት ናቸው።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አክሊሉ ታደሰ፤ ባለፉት ሁለት ዓመታት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርቶችን በስብጥር እንዲያመርቱ በርካታ ጥረት መደረጉን ተናግረዋል።

ከትናንት በስቲያ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠለት ቶፓን የተሰኘው ኩባንያ በዓመት አምስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ፓስፖርቶችን እንዲሁም 28 ሚሊዮን የሚሆኑ የተለያዩ ዲጂታል ካርዶችን የማምረት አቅም እንዳለው ተገልጿል።

የመሰረት ድንጋዩን የገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሽዴ፣ የብሔራዊ ባንክ ገዢው ማሞ ምህረቱ፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አብዱራህማን ኢድ፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አክሊሉ ታደሰ፤ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሰላማዊት ዳዊት፤ በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ሺባታ ሂሮሪ ከቶፓን ግራቪቲ ኩባንያ አመራሮች ጋር በጋራ አስቀምጠዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢንዱስትሪው ዘርፍ በቂ ድጋፍ እና ጠንካራ ክትትል ከተደረገለት ውጤታማ እንደሚሆን በተጨባጭ ታይቷል!

የለውጡ ኃይል መንግሥት ከሆነ ማግስት ጀምሮ ሀገሪቱን ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ማሸጋገር የሚያስችሉ የተለያዩ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፤ አሁንም እያደረገም ይገኛል። በዚህም እንደ ሀገር እየተመዘገበ ያለው ውጤት በብዙ መልኩ ተስፋ ሰጭ እንደሆነ መታዘብ እየቻልን ነው።

ለውጡ ገና ከጅምሩ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ካጋጠሙት ተግዳሮቶች አኳያ፣ በነፃ ህሊና ሁኔታዎችን ማየት እና መገምገም ለሚችል ሰው እውነታው ብዙም የሚያነጋግር አይደለም፣ ዓይን ከፍቶ በማየት ብዙውን ነገር መመስከር የሚቻልበት ሁኔታ ሰፊ ነው።

በተለይም መንግሥት ድህነትን ታሪክ በማድረግ ሀገር እና ሕዝብን ከጠባቂነት/ከተመጽዋችነት ለመታደግ ተግባራዊ እያደረገ ያለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ ሀገርን በከፉ ቀን ማሻገር የሚያስችል አቅም መገንባት አስችሏል፣ ለውጡ ብዙ ፈተናዎችን ተሻግሮ ዛሬ ላይ እንዲደርስ ጉልበት ሆኗል።

የፖሊሲው ዓላማ በዋነኛነት ለግብርና፣ ለቱሪዝም፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለዲጅታል ቴክኖሎጂ እና ለማዕድን ዘርፍ ስትራቴጂክ ትኩረት የሰጠ ፤ በየዘርፉ ያለውን አቅም በጥናት በማረጋገጥ አልምቶ ሀገር እና ሕዝብን ተጠቃሚ በማድረግ ብልጽግናን እውን ማድረግ ነው።

በተለይም ለኢንዱስትሪው ዘርፍ በፖሊሲው ውስጥ የተሰጠው ትኩረት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም ለዘመናት ከነበረበት ከግብር እና ከአገልግሎት ዘርፎች ወጥቶ በዋንኛነት በኢንዱስትሪ ላይ እንዲመሠረት ማድረግ የሚያስችል፤ ሀገሪቱ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለምታደርገው ጉዞ መንገድ ጠራጊ ተደርጎም የሚወሰድ ነው።

ለኢንዱስትሪው ዘርፍ በፖሊሲ ደረጃ የተሰጠው ትኩረት፤ ከዛም ባለፈ ሀገሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት በተሻለ መንገድ ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ለማዋል የተሻለ ዕድል የሚፈጥር፤ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን አምራች የሰው ኃይል ወደ ሥራ ለማስገባት ስትራቴጂክ አቅም የሆነም ጭምር ነው።

የኢንዱስትሪው ዘርፍ ስትራቴጂ፤ ሀገሪቱ በሁለንተናዊ መልኩ ማስመዝገብ ለምትፈልገው ልማት ትልቅ አቅም እንደሚሆን፤ በተለያዩ ምክንያቶች ለዘመናት ተቀዛቅዞ የኖረውን የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ዘርፍ በማነቃቃት ወደ አዲስ ምዕራፍ ማሸጋገር እንደሚያስችልም ይታመናል።

ይህን ታሳቢ በማድረግም መንግሥት ቀደም ሲል በዘርፉ ይስተዋሉ የነበሩ የቢሮክራሲ ችግሮችን ለዘለቄታው ከመፍታት ጀምሮ፤ ከፍተኛ ሀብት በመመደብ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በስፋት በመገንባት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ መሳተፍ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች የተመቻቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ይገኛል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ሶስት የግብርና ማቀነባበሪያዎች ተገንብተዋል። በቀጣይም ፍላጎቶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተጨማሪ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት ለዘርፉ መነቃቃት መንግሥት ዝግጁ መሆኑንም በተለያየ አጋጣሚዎች መግለጹ ይታወሳል፡፡

"ኢትዮጵያ_ታምርት እኛም_እንሸምት" በሚል መሪ ቃል ዘርፉን ለማነቃቃት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ሀገራዊ ንቅናቄው በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ያቆሙ፤ ከአቅማቸው በታች ሲያመርቱ የነበሩ ፋብሪካዎችን ችግር በመፍታት ወደ ምርት እንዲገቡ አስችለዋል፤ አዳዲስ ባለሀብቶችም ዘርፉን እንዲቀላቀሉ አድርጓል።

ንቅናቄው ዘርፉን ከማነቃቃት ባለፈ ፤ አምራች ኢንዱስትሪውን ከገበያ ጋር በማስተሳሰር ፤ ዘላቂ የሀገር ውስጥ ገበያ መፍጠር አስችሏል። ዜጎች በሀገራቸው ኢንዱስትሪዎች የሚመረቱ ሸቀጦችን እንዲያውቁ እና ጠንካራ የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩም መልካም ዕድል ፈጥሯል።

ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት ሀገርን ከከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ መታደግ አስችሏል። ለአብነትም ባለፉት 9 ወራት ከ1 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር በላይ ከውጭ ሀገር ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ተችሏል።

በሀገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች በዚህ ዓመት ብቻ "ኢትዮጵያ ታምርት እኛም እንሸምት" በሚል መሪ ቃል 83 የምርት ማስተዋወቂያ ኤክስፖዎች ተካሂደዋል፡፡ በእነዚህ ኤክስፖዎችም 3,223 ያህል አምራች ኢንዱስትሪዎች ተሳትፈውበታል፡፡ 10.78 ቢሊየን ብር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግም ዘርፉን አነቃቅተዋል።

በርግጥም በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊስ እንደተቀመጠው እና ተስፋ እንደተደረገው፣ ዘርፉ በቂ ድጋፍ እና ጠንካራ ክትትል ከተደረገለት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የላቀ ስፍራ እንደሚኖረው ሀገራዊ ንቅናቄ በተጨባጭ አሳይቷል። ይህንን እውነታ በአግባቡ ተረድቶ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ በዘርፉ የሚገኙ ተዋንያን የጋራ ኃላፊነት ነው!


# አዲስ ዘመን

እ ፕ ድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ መዳን ይችሳል ወይስ ይዳፈናል?

**ደፍሩ ብርሃን (ፕ/ር)**
**/ክፍል አንድ/**

ሚያዝያ 20 ቀን 2016 ዓ.ም NBC ኢትዮጵያ በተባለ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ ዶ/ር ደምሴ ታደሰ የተባሉ "የስኳር በሽታ የሚድን ነው" ብለው ሰፊ ውይይት የተደረገበትን፣ በyoutube ላይ የተጫነውን ቪዲዮ አይቸዋለሁ። በሥነ ምግብ ከማስተርስ እስከ PhD ያሉ ተማሪዎችን ከ10 ዓመት በላይ ሳማክር ስለቆየሁ ከስኳር በሽታና ሥነ ምግብ ጋር በተያያዘ ብዙ ምርምሮችን ስለምከታተል የውይይቱ ሃሳብ ሳበኝና ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ተነሳሳሁ። የአማርኛ ፊደላት አጠቃቀም ላይ የፈጠርኩት ግድፈት ካለ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

አንዳንድ የሕክምና ቃላቶችን ወደ አማርኛ መተርጎም አልቻልኩም። ካርቦሃይድሬት፣ ፕሮቲን እና ስብ (ፋት/ሊፒድስ) ለሚባሉት የምግብ ዓይነቶች ቀደም ብሎ የተሰጣቸው አቻ የአማርኛ ትርጉም በእጅጉ አሳሳች ስለሆነ (ኃይል ሰጭ የተባለው ካልተጠቀምንበት ገምቢም ስለሆነ፣ ገንቢ የተባለው በተወሰነ ደረጃ ኃይል ሰጭም ስለሆነ እና ስብ ምግቦች ለኃይል ምንጭነት ጭምር ስለሚውሉ) ካርቦሃይድሬት እና ፕሮቲን ሳይተረጎሙ እንዳሉ እንለማመዳቸው። ስንት አስቸጋሪ የታዋቂ ፈረንጆች ስም ስንይዝ መቼ ከበደን። Remission ለሚለው በትክክል የሚገልፅ የአማርኛ አቻ ትርጉም ስላጣሁ (ሌላ በሙያው ላይ ያለ ሲኒየር ሐኪም አማክሬ) "ማዳፈን" በሚለው ትርጉም ተስማምተናል።

ለፕሮግራሙ አዘጋጆች (ዶ/ር አበባ የሺጥላ እና ዶ/ር ይሁን አየለ) እና ተጋባዥ እንግዳ ለነበሩት ዶ/ር ደምሴ ታደሰ ምስጋና እያቀረብኩ፣ ሶስቱም ባለሙያዎች ሕዝብም ሆነ ባለሙያ አስተያየት እንዲሰጥበት ስለጋበዙ (ሃሳቡን ለአስተያየት ክፍት ስላደረጉት) እኔም በትንሹ አስተያየት መስጠት በቂ ሆኖ ስላገኘሁት ትንሽ ዘርዘር ያለ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ወሰንኩ። የዶ/ር ደምሴን አስተያየት በተወሰነ ደረጃ ብጋራም የማልስማማባቸው ትንሽ ጠንከር ያሉና ጅምላ አስተያየቶች ስላሉ አድማጮችን እንዳያሳስቱ ትኩረት ሊደረግባቸው በሚችሉት ነጥቦች ላይ የግል አስተያየቴን እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ።

ሁሉም ሰው ይህን የእኔን ጽሑፍ ከማንበቡ በፊት ውይይቱን ከyoutube ላይ ቢያይ ግንዛቤው ሙሉ ይሆናል። በውይይቱ ላይ የተገለፁ ብዙ ገንቢ ሃሳቦች በዚህ ጽሑፍ አልተካተቱም። ከሁሉ በፊት እንደዚህ ዓይነት ውይይት መጀመሩን ሳላደንቅ አላልፍም። ይህ የጤና ችግር የብዙ ሰውን ቤት አንኳኩቷል። ጥቂት የማይባሉ ሰዎች የተለያየ የማከሚያ መንገድ እያቀረቡ ሕዝቡን ለብይታ የዳረጉት አሉ። ስለዚህ ሳይንሳዊ እና አለማቀፋዊ የሆኑ የመከላከያ እና የማከሚያ ዘዴዎችን (Conventional prevention and treatment package) ሕዝቡ በግልፅ እንዲረዳ ሙያው የሚመለከታቸው ጭምር ርብርብ እንዲያደርጉ ለመጠቆም እኔም ይችን ጽሑፍ እንድታነቡልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ። ሕዝባችን በብዙ የጤና ችግሮች የሚጎዳው ስለ ጤናና ሕክምና በቂ ግንዛቤ ስለማያገኝ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለኝ።

በተለይ እንደ ዶ/ር አበባ ዓይነት (የጤና ባለሙያ የሆኑ ወይም በቂ ግንዛቤ ያላቸው አወያዮች) ቢበዙ የሚፈለገው ውጤት የሰመረ ይሆናል። የሕዝብ ቀዳሚ ችግር እየሆኑ በመጡት እና በብዙ መንገድ መከላከል በምንችላቸው የእድሜ ልክ በሽታዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ገና አልሰረፀም። ለብዙ አስርት ዓመታት ተላላፊ በሽታዎች ላይ ትኩረት አድርገን ስለቆየን፣ መንግሥትና የተባበሩት መንግሥታት ጭምር የምዕተ ዓመቱ እና የዘላቂ እድገት መለኪያ የተደረጉት በቀዳሚነት ተላላፊ በሽታዎች፣ የእናቶችና የልጆች ጤና ስለነበሩና አሁንም ስለሆኑ፣ ተላላፊ ያልሆኑ የጤና ችግሮች ወረርሽኝ በሚመስል መልኩ እየጨመሩ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ ሀገራችን የሁለቱም ችግር ገፈት ቀማሽ እንድትሆን አድርጓታል። በዚህ ላይ በምግብ እጥረት፣ በሱስ አምጭ እና ተጓዳኝ ችግሮች ከፍተኛ ተጠቂ ሆና እንደቀጠለች ነው።

ወደ ተነሳሁለት ርዕስ ስመለስ በመጀመሪያ ሁለተኛው ዓይነት (የአዋቂዎች) የስኳር በሽታ (Type II Diabetes Mellitus) በአብዛኛው በጎልማሳነት እድሜ ላይ ባሉ ሊዳፈን (Remission)፣ በተወሰነ ደረጃ ለረጅም ጊዜ ላይታይ (long-term remission) እንደሚችል በቂ ሳይንሳዊ መረጃዎች ስላሉ፣ የዶ/ር ደምሴ አስተያየት ከሞላ ጎደል ትክክል ቢሆንም ጨርሶ ሊድን (Cure) ይችላል የሚለው ገና ያልተረጋገጠ ነው። እስካሁን ባለው ሳይንሳዊ መረጃ፣ አንድ ሰው በወሰዳቸው ርምጃዎች ከምልክቶቹ ነፃ ሆነ ማለት ዳነ ማለት አይደለም (ዝርዝሩ ከታች ቀርቧል)። ይሁን እንጂ ሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ "የማይመለስና" እየጨመረ የሚመጣ (irreversible and progressive) የሚለው የቀደመ አስተሳሰብን የለወጡ እጅግ ብዙ መረጃዎች መውጣት ከጀመሩ ሰነባብተዋል፤ በተግባርም ከሰዎች እና ከሥራ ልምድ ማየት ተችሏል።

የዓለም ጤና ድርጅት እአአ በ2016 መረጃዎችን አሰባስቦ ሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ ማዳፈን እንደሚቻል ገልጿል። በእንግሊዝ የስኳር በሽታ ማህበርም የካሎሪ መጠናቸው በጣም ያነሰ ምግቦችን በመጠቀም፣ እንደዚሁ ካርቦሃይድሬት ምግቦችን በመቀነስ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግና በኦፕሬሽን ማዳፈን እንደሚቻል ድምዳሜውን አስቀምጧል። የአሜሪካ እና የአውሮፓ የስኳር ማህበራትም ሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ መዳፈን እንደሚቻል ካሳወቁ በኋላ ሙሉ በሙሉ ማዳፈን (Complete remission) ለሚለው ትርጉም ሰጥተዋል (ካለመድኃኒት ለ3 ወር የደም የስኳር መጠን ወይም ሌላው መለኪያ HbA1c ኖርማል ሆኖ መቆየት/Normoglycaemia መዳፈኑን ለማወጅ ያበቃል የሚል ነው)።

በዚህ መልኩ ለሕዝብ መግለፅ አመቺ ስላልሆነ እንጂ እጅግ ብዙ ሳይንሳዊ መረጃዎችን (ከ10 ዓመት በላይ ክትትል የተደረገባቸውን ጨምሮ) ማቅረብ ይቻላል። ስለዚህ ጉዳይ የመጀመሪያው ሳይንሳዊ መረጃ የወጣው እአአ በ1992 ነበር (በቀዶ ሕክምና ማዳፈን እንደሚቻል የተረጋገጠበት ጊዜ)። እአአ በ2008 እጅግ የላቀ በሚባለው ሳይንሳዊ የምርምር ዘዴ (Randomized controlled trial) የቀረበ ጥናት ማዳፈን እንደሚቻል ብዙዎችን ያሳመነ መረጃ አወጥቷል። ሌላው በውይይቱ ጊዜ ተጠቅሷል። ስለሆነም በተለይ በዚህ ዘመን ሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሳይደርስ ከብዙ ሰዎች ላይ ማዳፈን እንደሚቻል እጅግ ብዙ ሳይንሳዊ መረጃዎች ስላሉ የሳይንሳዊ መረጃ ክፍተት የለም። ትልቁ ነጥብ እንዴት ይቻላል የሚለው ነው (ከታች በጥቂቱ ተጠቁሟል)።

እንዲያውም (በውይይቱ ጊዜም እንደተጠቆመው) ከሕይወት ተሞክሮ ጭምር እጅግ ብዙ መረጃዎች ስላሉ፣ በዚህ ርዕስ ላይ የመገናኛ ብዙሃን በስፋት ቢሰሩ፣ በከተሞች

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ድርጅቱ 700 ሺህ ዜጎችን የበጎ ተግባራት ተጠቃሚ አድርጓል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ ዓመት በተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት ለ700 ሺህ ዜጎች ተደራሽ መሆን መቻሉን ኤስ.ኦ.ኤስ የሕፃናት መንደር አስታወቀ።

ኤስ ኦ ኤስ የሕፃናት መንደር 50ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን አስመልክቶ በትናንትናው እለት መግለጫ ሰጥቷል።

በመግለጫው ወቅት የኤስ.ኦ.ኤስ የሀገር ውስጥ ዳይሬክተር አቶ ሳህለማርያም አበበ እንደገለጹት፤ ድርጅቱ በዘንድሮ ዓመት በአስቸኳይ ጊዜ ሰብዓዊ ድጋፍ፣ በትምህርት፣ ወጣቶችን በማብቃት እና በአማራጭ የቤተሰብ ክብካቤ ለ700 ሺህ ዜጎች ተደራሽ መሆን ችሏል።

ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ ተቋሙ በተለያዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎች በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት ስምንት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዜጎች ተደራሽ መሆን ችሏል።

ተቋሙ በሀገሪቱ በዘጠኝ ክልሎች እየሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ሳህለማርያም፤ እ.ኤ.አ በ2027 በአክሱም፣ በደሴ፣ በሰመራ እና አርባ ምንጭ ተጨማሪ የማስተባበሪያ ጣቢያዎችን ለመገንባት ማቀዱን አስረድተዋል።

በሚገነቡት እና በነባር የማስተባበሪያ ጣቢያዎች የበጎ አድራጎት ተደራሾችን ቁጥር ከ700 ሺህ ወደ አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለማድረስ እቅድ ተይዟል። ለዚህም 210 ሚሊዮን ዶላር የሚያስፈልግ ሲሆን፤ እቅዱን ለማሳካት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የተለያዩ ገቢ የማሰባሰቢያ ሥራዎች በመሥራት ላይ ይገኛል ብለዋል።


አቶ ሳህለማርያም አበበ


ትብስት ሰለሞን (ዶ/ር)


አቶ ፋሲካው ሞላ

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የፖሊሲ እና ምርምር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ትብስት ሰለሞን (ዶ/ር) ሚኒስትሯን ወክለው ባቀረቡት መልዕክት እንደገለጹት፤ ሕፃናት የተሻለ ስልጠና አግኝተው በተሟላ የአመጋገብ ሥርዓት የሀገራቸውን እሴት ጠብቀው እና በራሳቸው ታሪክና ባህል ሊያድጉ ይገባል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ መመሪያዎች በመቅረጽ እና ተቋማዊ አሠራሮች በመዘርጋት ከፌዴራል እስከ ክልል ባለው መዋቅር እየሠራ ሲሆን፤ በሚሰሩ ሥራዎች መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን አንስተዋል።

ዶክተር ትብስት እንደገለጹት፤ ኤስ ኦ ኤስ ድርጅትም መንግሥታዊ ካልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አንዱ እንደመሆኑ፤ በተለያዩ ክልሎች አሳዳጊ የሌላቸውን ሕፃናት በማሳደግ፣ ወላጆችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎች በመሥራት ላይ ነው።

ሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ከኤስ ኦ ኤስ ተሞክሮ በመውሰድ ኢትዮጵያ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ለማደግ የምታደርገውን ጥረት እንዲደግፍ በማለት ጥሪ አቅርበዋል።

በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር አቶ ፋሲካው ሞላ በበኩላቸው፤ በጎ አድራጎት ድርጅቱ አሳዳጊ ሕፃናት በመልካም መንገድ በማሳደግ ለሀገር የሚጠቅም ፍሬያማ ትውልድ ማፍራት ችሏል።

በተጨማሪም የተለያየ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ አደጋ ሲደርስ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ከፍተኛ በጀት በመመደብ አፋጣኝ ምላሽ እየሰጠ ያለ ተቋም ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የበጎ አድራጎት ድርጅቱ በ50 ዓመት ጉዞ ያጋጠሙ ብርታቶች እና ጥንካሬዎች ቀምሮ በማስቀመጥ ለሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ተሞክሮ ሊሰጥ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

## የተጣለው የቪዛ ገደብ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ታሪካዊ ግንኙነት የማይመጥንና ጊዜውን ያልጠበቀ ውሳኔ በመሆኑ ገደቡ ሊነሳ ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት የዜጎቹ ክብርና ማንነት ተጠብቆ ወደሀገራቸው እንዲመለሱ ብሔራዊ ኮሚቴ አዋቅሮ ከኅብረቱ ጋር እየሠራ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ በሂደቱ ላይ የሚያጋጥሙ ጉዳዮችም ካሉ ለመነጋገርና ዓለም አቀፍ መርህን ተከትሎ መፍትሔ ለመስጠት ኢትዮጵያ ዝግጁ እንደሆነች ጠቁመዋል።

ከዚህ ቀደም ወደ አውሮፓ የጉዞ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም አመልካች ተገቢ ሰነድ አሟልቶ በ15 ቀናት ያጠናቅቅ የነበረውን የቪዛ ፈቃድ ሂደት ወደ 45 ቀን ከፍ የሚያደርገው ውሳኔ ኢ-ፍትሐዊና ጊዜውን ታሳቢ ያላደረገ እንደሆነ ቃል አቀባዩ ገልጸው፤ ውሳኔው ትክክል እንዳልሆነ መንግሥት ለኅብረቱ አሳውቋል ነው ያሉት።

ኅብረቱ 89 ዜጎች ኢትዮጵያዊ እንደሆኑ ቢያሳውቅም 26ቱ ብቻ የኢትዮጵያዊ ዜግነት እንዳላቸው እንደተረጋገጠ ጠቅሰው፤ 15ቱ ወደ ሀገራቸው እንደተመለሱና የተቀሩትን የመመለሱ ሂደት እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

ተቀማጭነታቸውን አዲስ አበባ ያደረጉ የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች የሚያወጧቸው የደቦ መግለጫዎች ከተለመደው የዲፕሎማሲ አሠራር ያፈነገጡ በመሆናቸው ኢትዮጵያ እንደማትቀበል ገልጸው፤ የዓለም የፕሬስ ቀንን አስመልክቶ ያወጡት መግለጫ ተገቢነት እንደሌለው አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፕሬስ ነፃነትን ለማፅናት የመገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ማቋቋምን ጨምሮ የተለያዩ አዋጆችን ማፅደቁን ተናግረው፤ መንግሥት የፕሬስ ነጻነትን ለማረጋገጥ ጽኑ አቋም እንዳለው ቃል አቀባዩ ተናግረዋል ።

አቶ ነቢዩ፤ በሳምንቱ ከተከናወኑ አበይት ዲፕሎማሲያዊ ሁነቶች መካከልም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ልዑካን ቡድናቸው ናይሮቢ ኬንያ በተካሄደው የዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ጉባዔ ላይ ተሳትፈው ጠቃሚ መልእክት ማስተላለፋቸውንም ገልጸዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ ከኤልሳቫዶር አቻቸው ኤሌክሳንድራ ሂል ቲኖኮ ጋር ውይይት ማድረጋቸውን ያነሱት አቶ ነቢዩ፤ ኤል ሳቫዶር በኢትዮጵያ ኤምባሲ ልትከፍት ማቀዷ የአዲስ አበባን የዲፕሎማሲ ማዕከልነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ለመምጣቱ ተጨማሪ ማረጋገጫ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንዲሁም ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የሀገር ውስጥ መፈናቀል መፍትሔዎች ልዩ አማካሪ ሮበርት ፓይፐር ጋር ባደረጉት ውይይት፤ ኢትዮጵያና ተመድ ትብብራቸውን ለማሳደግ መስማማታቸውንም ቃል አቀባዩ አንስተዋል።

በተጨማሪም አምባሳደር ምስጋኑ ከሱዳን ሪፐብሊክ ተጠባባቂ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ሁሴን አዋድን ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት፤ አምባሳደር ሁሴን ኢትዮጵያ በሱዳን ሁለንተናዊ የሰላም ማስፈን ሂደት ውስጥ እየተጫወተች ያለውን ወሳኝ ሚና አጠናክራ እንድትቀጥል መጠየቃቸውን ገልጸዋል።

## ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋን የሚሸከም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የባሕርበር የራሴ ነው” በሚል እርግጠኛ መሆን የሚቻልበትን መንገድ መፍጠር ያስፈልጋል ሲሉ አስረድተዋል።

ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመውጣት ጠንክሮ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ሊቀመንበሩ፤ በአሁኑ ወቅት ከባህር በር ጋር ተያይዞ የጂቡቲ መስመር አንድ ነገር ቢሆን ይህ ብቻውን የማያስተኛ ስጋት መሆኑ ሊታበል አይገባውም ብለዋል።

ሊቀመንበሩ እንደገለጹት፤ የባህር በር ማጣት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል።

ከዚህ በኋላም ኢትዮጵያ ባለችበት የባህር በር እጦት የምትቀጥል ከሆነ ጉዳቱ እየሰፋ መሄዱ ስለማይቀር አማራጮችን ማስፋት ተገቢ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት ቀርቶ የእራሳቸው ወደብ ያላቸውም አማራጭ የባህር በሮችን አልምተው ጥቅም ላይ ያውላሉ ያሉት ሊቀመንበሩ፤ ሳውዲ አረቢያ በተለያዩ ቦታዎች ወደብ ያላት መሆኑን ለአብነት አንስተዋል።

ከኢኮኖሚው ባለፈ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የእራሷ ወደብ ቢኖራት ለቀጣናው ሰላም መረጋገጥ የበኩሏን አስተዋጽኦ መወጣት የምትችል ሀገር መሆኗን ፕሮፌሰር በየነ ተናግረዋል።

የባሕር በርን በተመለከተ ኢትዮጵያ ሥራዋን መቀጠል


በየነ ጴጥሮስ (ፕ/ር)

አለባት ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ለቀጣዩ ትውልድ የተረጋጋች እና ከስጋት ነፃ የሆነች ሀገርን ለማስረከብ በተነደፈው ዕቅድ ላይ መጠንከር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

## በኢትዮጵያ የካፒታል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የፋይናንስ ዘርፉ በ2024 መጀመሪያ ላይ ጠንካራና ተከታታይ ዕድገት አሳይቷል ያሉት አቶ ማሞ፤ 121 የፋይናንስ ተቋማት ሦስት ነጥብ አራት ትሪሊዮን ሀብት፣ ሁለት ነጥብ አራት ትሪሊዮን ተቀማጭ እና ሁለት ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብድር አግኝተዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በፋይናንስ ዘርፉ መረጋጋት፣ ማካተትና ዘመናዊነት ላይ ያተኮረ ተስፋ ሰጪ አጀንዳን እየተገበረች መሆኑን ገልጸው፤ የፋይናንስ ተቋማት የሥራ ደረጃቸውን ማሳደግና ዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀበል እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ለውጭ ባለሀብቶች መከፈቱ ፈጠራንና ውድድርን ለማፋጠን የሚያግዝ መሆኑን ገልጸው፤ የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች አዲስ ካፒታል እና አዳዲስ ምርቶችን በማምጣት ዓለም አቀፍ ምርጥ ልምዶችን እንደሚያስገኙ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ማሻሻያ ብሪክስ-ፕላስ ቡድን ከመግባቷ ጎን ለጎን እየተካሄደ ነው ያሉት አቶ ማሞ፤ አዳዲስ ኢኮኖሚያዊ አጋርነቶችንና የገንዘብ ድጋፍ መንገዶችን ለመክፈት የካፒታል ተደራሽነት፣ የኢንቨስትመንት ዕድሎችና የትብብር ልማቶችን ይፈጥራል ብለዋል።

በጂኦ ፖለቲካው መድረክ እንደ ብሪክስ ያሉ አዳዲስ ቡድኖች መፈጠር ለፋይናንስ አደጋዎችና እድሎች እየፈጠሩ መሆኑን በመግለጽ፤ ዓለም አቀፋዊ ጫናን ለመቋቋምና ለመቆጣጠር ጠንካራ ምላሽ ሰጪ የፋይናንስ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የአይ ካፒታል አፍሪካ ኢንስቲትዩት ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ገመቹ ዋቅቶላ በበኩላቸው፤ በጉባኤው የፋይናንስ አካታችነት፤ የቀጣናው የኢኮኖሚ ጉዞ እና የኢትዮጵያ ትግበራ ይዳሰሳል ብለዋል።

ጉባኤው የፋይናንስ ዘርፉን የወደፊት አቅጣጫ ለማመላከት የሚረዳ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ገመቹ፤ በፋይናንስ ዘርፉ ያሉትን ፖሊሲዎች ሕግና ደንብ ለማጥራት እና አቅጣጫን ለማመላከት ይረዳል ብለዋል።

የፋይናንስ አካታችነት፤ የቀጣናው የኢኮኖሚ ጉዞና የኢትዮጵያ ትግበራ በጉባኤው እንደሚዳሰስ ጠቅሰው፤ የካፒታል ገበያ፣ የዲጂታል ፋይናንስ ጉዞ፤ የፋይናንስ ገበያ ሊበራላይዜሽን ዙሪያ ምክክር እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ጉባኤው ለሀገሪቱ አጠቃላይ የፋይናንስ ጉዞ መፍትሔ እንደሚያዋጣ አብራርተዋል።

በጉባኤው የፖሊሲ አውጭዎችና አጥኚዎች የጥናት ጽሑፎች እንደሚቀርቡም ጠቁመዋል።

በመድረኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱን ጨምሮ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ተጠሪ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ የመንግሥትና የግል ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## “ኢትዮጵያን በተሻለ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በመጠቀም በጋራ ማደግ ይገባል።

ስንዴ አምርተን መጀመሪያ መብላት፣ ቡና አምርተን መጀመሪያ እኛው መጠቀም እንዳለብን ሁሉ ልብስ አዘጋጅተንም መጀመሪያ የሀገሬውን ሰው ማልበስ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

በኢትዮጵያ በ120 ሚሊዮን ሕዝብ ልክ ገበያ እያለ ብዙዎች ግን የተለያዩ ምርቶችን ከውጭ የሚያስገቡበት አግባብ ስህተት መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ አምርታ ከምትልከው ይልቅ ከውጭ የምታስገባው ምርት ተመን በቢሊዮን ዶላሮች እንደሚልቅ ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አልባሳትን ለአብነት በማንሳት በሀገር ውስጥ ጥራትና ውበት ያላቸው ምርቶች በመኖራቸው እኔም እየተጠቀምኩ ነው ብለዋል። ስለዚህም በሀገር ውስጥ ያለን ምርት መጠቀምን መለማመድ ይኖርብናል ሲሉ አስረድተዋል።

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኢንዱስትሪዎች ጨርቃ ጨርቅ አምርተው ወደውጪ መላክ ላይ ብቻ ከማጠንጠን ምርቱ በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድ ላይም መሥራት እንዳለበት አመላክተዋል።

በአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች የቡና ምርታማነት ቢጨምርም እንደኢትዮጵያ ካሉ የቡና አምራቾች ይልቅ ቡናና ወተትን እያቀላቀሉ ቸኮሌት የሚሠሩ ሀገራት የተሻለ ገቢ እንዳላቸው አንስተው፤ በኢትዮጵያም የተሻለ ገቢ ለመፍጠር በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋትና ግብዓቶችን በሰፊው መጠቀም እንደሚገባ አመላክተዋል።

ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን በስፋት አዘጋጅተናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አምራች ኢንዱስትሪዎችም በግብዓት፣ በኢነርጂ፣ በገበያና በሰው ኃይል ኢትዮጵያ ያላትን አቅም በተሻለ ወደ ውጤት ለመለወጥ መትጋት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት አንድ ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር የሚያወጡ ተኪ ምርቶች ለገበያ መቅረባቸውን አስታውቀው፤ የሀገር ውስጥ አምራቾችን በመደገፍ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የተገኙ ውጤቶችን ማስቀጠል እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በተለያዩ ዘርፎች የተገኙ ውጤቶች አበረታች መሆናቸውን አንስተው፤ ለውጡ ሲመጣ የኢትዮጵያ ጥቅል ሀገራዊ ምርት ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ሁለተኛው ነበር ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አሁን ላይ ግን የጎረቤት ሀገራት ጥቅል ሀገራዊ ምርት ቢደመር የኢትዮጵያን አያክልም ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪ መንግሥት ወደኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚቀላቀሉ ምቹ ሁኔታን ማዘጋጀቱን ጠቁመው፤ አምራቾች በበኩላቸው በሀቀኝነት ግብራቸውን በመክፈል ግዴታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር መላኩ አለበል በበኩላቸው፤ በ2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ 210 የተለያዩ ድርጅቶችና ጥሪ የተደረገላቸው 50 የውጭ ባለሀብቶች እንደሚሳተፉበት ጠቁመው፤ ከሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት እንደሚፈጸምበት ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢንዱስትሪ ዘርፉ በዘንድሮው ዓመት ከ256 ሺህ በላይ የሥራ ዕድል መፍጠሩን ገልጸው፤ በትብብር መስራት ከተቻለ የተሻለ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣ ሚኒስትሮች፣ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በኤክስፖው የቀረቡ ምርቶችን ጎብኝተዋል። የ2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ እስከ ግንቦት 5 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ለሕዝብ ክፍት ሆኖ ይቆያል።

# ስታርት አፕን ለሀገራዊ እድገት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




ስታርት አፕ ሲባል ማንኛውም በአነስተኛ ደረጃ የተጀመረ የሥራ መስክ ማለት አይደለም። ስታርት አፕ ሃሳብ በፈጠራ ሃሳብ (ኢኖቬቲቭ አይዲያ )ቴክኖሎጂን ተንተርሶ አንድን ችግር ለመፍታት የሚቋቋም ዘር ማለት ነው። ቴክኖሎጂን ካልተጠቀመ የፈጠራ ሃሳብ ከሌለ እና የሚፈታው ችግር ከሌለ ሥራ መጀመር ብቻ ስታርት አፕ አያስብለውም።

ስታርት አፕ ማለት ይሄ ነው ካልን በኋላ ግን ይሄ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይም አዲስ ቋንቋ ነው ከቴክኖሎጂ ውልደት እና መብዛት ጋር ተያይዞ የመጣ እሳቤ ነው። የቆየ ቀደም ሲል የሚነገር ቋንቋ ሳይሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓለም ላይ እየተነገረ የመጣ ቋንቋ ነው በእኛም ሀገር ከጠቀሜታው አንጻር ስታርት አፕ የሚሉ ቋንቋዎች በመጠኑም ቢሆን እየተነገሩ መጥተዋል።

ብዙ ጊዜ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚፈጠሩ ሥራዎችን የሚፈጥሩት ሁለት እና ከዛ በላይ ሰዎች ናቸው። የአፈጣጠር ባህሪው እራሱ የቡድን ሥራ በጋራ የመሥራት ባህሪ እና ዝንባሌ አለው፤ እስካሁን በታየው ልምድ ዓለም ላይ ስኬታማ የሆኑ ስታርት አፖች ዕድሜያቸው በአማካይ ከሠላሳ አምስት እስከ አርባ የሚደርሱ ሰዎች ናቸው። በስታርት አፕ የተሳካላቸው የሚባሉት እነዚሁ ነበሩ ።

ስታርት አፕ ላይ ለሚሳተፉ ሃሳብ አለን የሚሉ ትናንሽ ተቋማት መፍጠር እንችላለን ማደግ እንችላለን የሚሉ ወጣቶች ግን አሁን አሁን ብቅ እያሉ በዘርፉም ስኬትን እየተቆናጠጡ ነው። ነገር ግን እነዚህ ወጣቶች ወደ ሥራ ፈጠራው መግባታቸው በጣም ጥሩና የሚበረታታ እንደ ሀገርም ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም ያሰቡበተ ስኬት ላይ ለመድረስ ግን መጀመሪያ አራቱን የ“መ” መርህዎችን (ፕሪንሲፕል) መከተል ወይም ማሟላት ይኖርባቸዋል። እነዚህን አላሟሉም ማለት ግን ሥራውን ቢጀምሩትም ስኬት ይሉት ደረጃ ላይ መድረሱ አስጊ ነው የሚሆነው። አራቱን “መ” ዎች ካላሟሉ ግን ከ 90 በመቶ በላይ ስኬታማ ነው የሚሆኑት ።

### አራቱ “መ“ዎች ምንድናቸው?

የመጀመሪያው ሊሰሩት ያሰቡትን ነገር ሐሳብ “መውደድ” ነው ፍቅሩ አለኝ? ወይ እወደዋለሁ ወይ? የሚለውን ነገር ለራሳቸው መመለስ ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም ሰው የሚወደውን ነገር ሲሰራ አያደክምም። አይሰበርም፣ መከራን ቢያሸክመውም እንኳን አይከብደውም ስለዚህ መጀመሪያ መውደድን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ሁለተኛው ደግሞ መውደድ ብቻውን በቂ ስላልሆነ “መቻል’’ ያስፈልጋል። ሥራውን እችለዋለሁ ወይ? የሚለውን መመለስም ግድ ነው። ለምሳሌ አውሮፕላን በአየር ላይ ሲሄድ አይተህን በጣም ደስ ይለናል ግን አውሮፕላን መሥራት እንደምንችል ካላሰብን መተው ነው ያለብን እኔ ሃሳብ አለኝ ምናምን ማለት ውጤታማ አያደርግም። ከመውደድ ቀጥሎ መቻልንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

መውደድ እና መቻል በቂ ስላይደሉ ሶስተኛው ስታርት አፕን ስኬታማ የሚያደርገው ነገር “መፈለግ’’ ነው። ያ የምንወደው እና የምንችለው ነገር በማርኬቱ በገበያው በሕዝብ ይፈለጋል ወይ? ገበያ አለው ወይ? ሰዎች የሚያደምጡት የሚፈልጉት የሚገዙት ነገር ነው ወይ? የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል።

አራተኛው “መሸጥ’’ ነው ገንዘብ ማምጣት ነው። መውደድ፣ መቻል፣ መፈለግ፣ መሸጥ። እነዚህን አራት "መ" ዎች ማሳካት እንግዲህ በስታርት አፕ ሂደት ላይ ስኬታማ እንደሚያደርግ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወደ ሀገራችን መለስ ስንል ሀገራችንም በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል እንዳላት የሚያመላክቱ ነገሮች ያሉ ሲሆን እነሱንም እውን ለማድረግና ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት እያደረገች ትገኛለች። ለምሳሌ የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል፣ ዘመናዊ ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ግብርናን ዘመናዊ በማድረግ በምግብ ራስን ለመቻል፣ ለጤና ብሎም በወታደራዊ አገልግሎት ላይ ውጤታማ ለመሆን ቴክኖሎጂ መሠረታዊ ነገር መሆኑም ገብቶን ወደ ሥራ ገብተናል።

የቴክኖሎጂ አቅም ማደግም ከሀገር ውስጥ አገልግሎትን ከማሻሻል አንስቶ በውጭ ሀገራት ለሚገኙ በዚህ ዘርፍ ያሉ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶችን ለማሟላት የራሱን አስተዋፅኦ የሚያደርግ ነው። አሁን ላይ ኢትዮጵያ ለቴክኖሎጂ ልማት ሰፊ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች መሆኑን በመንግሥት ተደጋግሞ ይገለፃል። የዚሁ አካል የሆነ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርም ከመጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ለሶስት ሳምንት ያህል ‹‹ስታርት አፕ ኢትዮጵያ›› በሚል ዓውደ ርዕይ ሲካሄድ ሰንብቷል። በዓውደ ርዕዩም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በግብርና፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በፋይናንስና በሌሎች ዘርፍ የተሰማሩ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ‹‹ስታርት አፖች›› ሥራዎቻቸውን አስተዋውቀዋል፤ እንደ ሀገርም ቴክኖሎጂን መሠረት ባደረጉ የሥራ ፈጠራዎች ላይ የደረስንበትን ደረጃ የሚቀሩንን ሥራዎች ለማየትና ለመታዘብ ችለናል።

በእለቱ በርካታ ወጣቶች በቴክኖሎጂው ዘርፍ ሥራን ፈጥረው ለውጭ ሀገራት ካምፓኒዎች በማገልገል ዶላር የሚያመጡ ወጣቶች መኖራቸውንም አይተናል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም አሜሪካ ውስጥ ለሚገኘው "ማክዶናልድ" ለተባለ ምግበ አቅራቢ ተቋም የሚሰሩ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች መኖራቸውን በ‹‹ስታርት አፕ ኢትዮጵያ›› ዓውደ ርዕይ ላይ መክፈቻ ላይ ተናግረው አረጋግጠዋል። ታዲያ ይህን ተስፋ ሰጪ ጅምር ከግቡ እንዲደርስ ሰዎችን የማብቃት ሥራው ተጠናክሮም መቀጠል ያለበት ነው።

በየዓመቱ የሚመረቁ የሶፍትዌር ኢንጂነሮች፤ የአይቲ ባለሙያዎችም የዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ያለን ሥራ በመሥራት በሀገራቸው ተቀምጠው ራሳቸውን ጠቅመው ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪን እንዲያስገኙም ማበረታታቱ ከዚህ መጀመር አለበት ። በሌላ በኩል ደግሞ በሀገር ውስጥ ያሉ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ሀገሪቱ ያላትን ርካሽ የሰው ጉልበት በመጠቀም የሥራ አጦችን ቁጥር መቀነስ ይቻላል። የሀገራችን የሰዓት አቆጣጠራችን ለብዙ ሀገራት የተመቸ መሆኑ፤ በቴክኖሎጂው የሰለጠኑ ወጣቶች መበርከታቸው በተወሰነ ስልጠና ለገበያው የተስማሙ ብቁ አቅም ያላቸው ወጣቶች መኖራቸው የውጭውን ፍላጎት ለመያዝ ያስችለናል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቴክኖሎጂው ዓለም ውስጥ በርካታ እቅም ያላቸው፤ የቴክኖሎጂ እውቀታቸው የላቀ ወጣቶች እየተፈጠሩ ነው ወጣቶች ቴክኖሎጂን የመረዳት አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑ ለዚህ አስተዋፅኦ አድርጓል።

አሁን ያለው የትምህርት ሁኔታ በተለይም በከተማ አካባቢ ወጣቶችን የሚያበቃ ነው። ከዚህ አንጻር ከቴክኖሎጂ አንድ ነገርን ይዞ በትእግስት የመጨረስ አቅም ያላቸውን ወጣቶች እያፈራን ነው። ወጣቶች ይህንን ሥራ መሥራታቸው በራሱ ሌላ አቅም የሚፈጥር ሆኗል።

በሚገርም ሁኔታ ወጣት ሴቶች እንኳን አግብተው፤ ወልደው ቤት ውስጥ ሆነው መሥራት የሚችሉበት የቴክኖሎጂ ሥራ ነው። በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ትምህርት ማግኘት በእጅ ያለ ስለሆነ በስልክ መማር እና መሥራት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።

በሀገሪቱ በርካታ ሶፍትዌር ኢንጂነሮች መገኘታቸው፤ ሥራ ፈጣሪዎች መበራከታቸው፤ በቀደመ ጊዜ ከነበረው በተለየ ለቴክኖሎጂ ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ መስክ ወደፊት እንደምትራመድ አመላካች ነው።

ከታላላቆቹ እኩል መራመድ እንችል ዘንድ፤ እየተፈጠረ ያለውን የቴክኖሎጂ ግብዓት የታጠቀ ትውልድ ማፍራት አስፈላጊ ነው። ስለዚህም አሁን ስታርት አፖችን ለማበረታታት የተወሰደው ዓይነት ገንቢ አስተዋጽኦ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ይህ የስታርት አፕ ሥራ በሀገራችን እውን ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተናገሩት ይህንን ነው፤" እንደ መንግሥት በፈጠራ ላይ የተመሠረተና የመፍትሔ ሃሳብ ያላቸውን ‘ስታርት አፖች’ መደገፍ ኢንቨስትመንት እንጂ ርዳታ አይደለም “ስታርት አፕ” ማለት ማንኛውም ሥራ ሳይሆን በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ፣ ገቢ የሚያመነጭ እንዲሁም ለአንድ ጉዳይ መፍትሔ ያለው አዲስ የሥራ ፈጠራ ነው። ስታርት አፖችን መደገፍ ከቻልን የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ" ብለውም ነበር።

የግብር ገቢንም ማሳደግ ይቻላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እንደ መንግሥት በጋራ ጥቅም ላይ በመመስረት በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ ሃሳቦች ወደተግባር እንዲወርዱ የተለያዩ ሥራዎችን አከናውነናል፤ በቀጣይም እናከናውናለን። በዓለም ላይ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ሀብት ያላቸው አንድ ሺህ 200 ስታርት አፖች አሉ፤ በአጠቃላይ ሀብታቸው አራት ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ደርሷል። ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን አንድ ቢሊዮን ዶላር ሀብት ያለው ስታርት አፕ አለመፈጠሩንና ጉዳዩ በጅማሮ ላይ ያለ መሆኑን መዘግየትን ቢያመለክትም። ከአምስት ዓመታት በፊት በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ 50 ስታርት አፖች መኖራቸውን ግን ማስታወስ እንደሚገባ አነስተዋል፤ አሁን ላይ ግን ቁጥራቸው 900 መድረሳቸውና ከቁጥር ዕድገቱ ባለፈ በተለያዩ መስኮች ላይ የተሰማሩ መሆናቸው እንደሀገር ተስፋ የሚሰጥ መሆኑን ተናግረዋል። መንግሥት በፖሊሲ፣ የቴክኖሎጂ ማዕከላትን በማስፋፋት እንዲሁም ምቹ አሠራርን በማስተዋወቅ ስታርት አፖችን ለማበረታታት ሰፊ ሥራ እያከናወነ ነው።

የፈጠራ ሥራዎቹ ግን በዋነኛነት በግሉ ዘርፍ እንጂ በመንግሥት የሚከናወኑ ባለመሆናቸው ሁሉም የበኩሉን ጥረት ሊያደርግ ይገባል ሲሉም ነበር መልዕክታቸውን ያስተላለፉት። ወጣቶች አዲስ ፈጠራ ሲጀምሩ በቅድሚያ ሥራውን መውደድ፣ ቀጥሎም ሥራውን በራሱ መቻላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ፈጠራው ተፈላጊና በገበያ ላይ ሊሸጥ የሚችል መሆኑን ማወቅ አለባቸው ሲሉ አስረድተዋል። ወጣቶች ትልቅ አስበው ከትንሽ በመነሳት ለሀገር የሚተርፍ የፈጠራ ሥራ ማከናወን እንዲሁም ውስጣቸው ያለውን ችግር ፈቺ የፈጠራ ሃሳብ ወደተግባር በማዋል ገቢ መፍጠር እንዳለባቸው አመላክተዋል።

የስታርታፕ አውዱ ጅማሮ ላይ ቢሆንም ችግሮች ግን የሉበትም ማለትም አይደለም ፤ የኢንተርኔት ዋጋ፣ የቢሮ ኪራይ፣ የኤሌክትሪክ ዋጋው ሲታይ ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ለስታርት አፖች ውድ ቢሆንም በጋራ በመደጋገፍ ስኬታማ መሆን ይቻላል። ከለውጡ በፊት በቴክኖሎጂ የተደገፈ የፋይናንስ አገልግሎት (ፊንቴክ) የሚያከናውን ካለ በሕግ ደረጃ ወንጀለኛ ሆኖ ተጠያቂ ይሆን ነበር ፤ አሁን ላይ ግን በርካታ ተቋማት በዘርፉ ተሰማርተው ገንዘብ እያንቀሳቀሱ ይገኛሉ። መንግሥት ስታርት አፖችን መደገፍ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘቡ የተለያዩ ማበረታቻዎችን እያደረገም ነው።

# የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናትን እሴት ጨምሮ ለገበያ የማቅረብ ውጥን

**ወርቅነሽ ደምሰው**



ኢትዮጵያ እንደ ኦፓል፣ ኤመራልድ፣ ሳፋየር፣ ሩቢ፣ አጌት እና ኳርትዝ የመሳሰሉ በዓለም ላይ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት እምቅ ሀብት ያላት ሀገር ነች። ይሁን እንጂ እስካሁን ሀገሪቱ ያላትን እምቅ የማዕድን ሀብቶች በማልማት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን እንዲያስገኙ በማድረግ ረገድ የተሠሩ ሥራዎች እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም። በተለይ መኖራቸው እንኳን በጥናት የተረጋገጡት የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት በማልማት የውጭ ምንዛሪ ከማግኘት አኳያ የሚደረጉ ጥረቶች እምብዛም ውጤት እያስገኙ እንዳልሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በዓለም አቀፍ ደረጃ በከበሩና በጌጣጌጥ ማዕድናት ዘርፍ በዓመት 250 እስከ 300 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሀብት ይንቀሳቀሳል። በኢትዮጵያም እስከ አለፈው ዓመት ድረስ ከ3 እስከ 4 ሚሊዮን ዶላር ሀብት ያስገኘ ነው። ይህም የሚያሳየው የዓለምን ኢኮኖሚ እያንቀሳቀሰ የሚገኘውን ሀብት በሚገባ ለመጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎች ከተሠራ አመርቂ ስኬቶችን ማግኘት እንደሚቻል ነው።

ከባለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን በመንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶት ሥራዎች በመሠራታቸው አበረታች ለውጦች እየታዩ ነው። በተለይ ደግሞ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ለውጭ ገበያ በመላክ ለኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንዲውሉ የማልማት ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በአሁኑ ወቅት የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን እንዲያመጡ እየተደረገ ይገኛል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን የሚበልጠውን ገበያ የያዙት ምንም ዓይነት እሴት ሳይጨመርባቸው በጥሬው የሚላኩት ማዕድናት ናቸው።

የዘርፉን የአምስት ዓመታት የውጭ ገበያ መረጃ ይህንኑ የሚያመላክት ነው። በአምስት ዓመታት ለውጭ ገበያ ከተላኩት የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት 95 በመቶ ያህሉ በጥሬው (ምንም ዓይነት እሴት ሳይጨመርባቸው) እየተላኩ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ አምስት በመቶ ያህሉ ብቻ እሴት ተጨምሮባቸው የሚላኩ መሆኑን ነው።

ይህም ሀገሪቱ ያላትን የማዕድን ሀብት በማልማት ከማዕድናቱ ማግኘት የሚገባት የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ ብዙ ሥራዎች መሥራት እንደሚጠይቅ ያመላክታል። በተለይ በዚህ ዲጂታል ዘመን ያደጉ ሀገራት የደረሱበት ርቀት ላይ ለመድረስና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችሉ አማራጮችን መጠቀምን ይጠይቃል። ለዚህም በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት ብዙ ይጠበቃል።

በማዕድን ዘርፉ ተሰማርተው ሀገሪቷ ያላትን የማዕድን ሀብት ለማስተዋወቅ እየሠሩ ካሉ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን አንዱ ነው። ኮርፖሬሽኑ ላለፉት 80 ዓመታት በማዕድን ዘርፍ ተሰማርቶ እየሠራ የቆየው ሲሆን፤ የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት በዓለም እንዲተዋወቅና ደረጃቸውን የጠበቁ የማዕድናት ጌጣጌጦች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲመረቱ ለማድረግ እየሠራ ይገኛል።

ኮርፖሬሽኑ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅ እና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሲሆን፤ የስም ለውጥ አድርጎ የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 462/2012 እንደገና የተቋቋመ የልማት ድርጅት ነው። የተቋቋመበት ዓላማም በማዕድን፣ በነዳጅና በባዩ ፊውል ሥራዎች፣ ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት በተገቢው ሁኔታ በማልማት ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል ነው።

የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን ተወካይ ዳይሬክተር አቶ አሕመድ አባጊሳ እንደሚሉት፤ የኢትዮጵያ ማዕድን ኮርፖሬሽን በማዕድን ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ እየሠራ ያለ የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው። ኮርፖሬሽኑ በማዕድን ዘርፍ የማዕድናት ፍለጋና ቁፋሮ፣ ማዕድናትን መመርመርና መለየት፣ የከበሩ ማዕድናት ለገበያ ማቅረብና እሴት ጨምሮ ወደ ውጭ መላክ፣ ለዘርፉ ስልጠናዎች መስጠት እንዲሁም ማማከር እና መሰል ሥራዎችን ይሰራል።

ኮርፖሬሽኑ ያለው ረጅም ዓመታት ልምድ በመጠቀም የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት እያደረገ መሆኑን አቶ አሕመድ ያመላክታሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የተለያዩ ለውጦች በማድረግ በዘርፉ ይበልጥ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን አንስተዋል። ኢትዮጵያ ያላት የማዕድን ሀብት መጠቀም እንድትችል በበኩሉን ድርሻ ለመወጣት በርካታ ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል። በተለይ የከበሩ ማዕድናት ላይ እሴት ጨምሮ የውጭ ምንዛሪን ከፍ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ለዓለም በማስተዋወቅ በዲጂታል ገበያ አማካይነት ማዕድናት ለገበያ በማቅረብ ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባት የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ እንዲሁም ሕገ ወጥ የማዕድን ዝውውር ለማስቀረት ጥረት እየተደረገም መሆኑንም አመላክተዋል።

‹‹ኮርፖሬሽኑ በሰው ኃይል እና በቁሳቁስ ቀደም ሲል ከነበረው በላይ በማጠናከር በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ በመንግሥት ኃላፊነት ተሰጥቶት እየሠራ ነው›› ያሉት አቶ አሕመድ፤ ወርቅ፣ ታንታለም፣ የከበሩ ማዕድናት፣ ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት እና ሌሎች በርካታ ማዕድናት ዓይነቶች ብዙ ሥራዎችን እንደሚሰራ አስታወቀዋል። በተለይም በኢትዮጵያ በሚገኙ የከበሩ ማዕድናት ኦፓል፣ ኤመራልድ፣ ሳፋየር እና ሌሎች ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ለማቅረብ ጥረቶች እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል። አሁን ላይ ኦፓል ማዕድን ላይ በስፋት የተሠራ መሆኑን ጠቅሰው ፤ ሌሎችም ከዚሁ ጋር ተያያዥ የሆኑ የከበሩ ማዕድናት ላይ ብዙ ተግባራትን ለማከናወን ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ኮርፖሬሽኑ በሙያ የሰለጠኑ ብቁ ባለሙያዎች እና አስፈላጊ የሆኑ ማሽኖች አሟልቶ የያዘ የከበሩ ማዕድናት የማበልጸጊያ ወርክሾፕ ያለ መሆኑን የገለጹት አቶ አሕመድ፤ በወርክሾፑ የከበሩ ማዕድናትን በመቅረጽ ደረጃቸው የጠበቁ ጌጣጌጦችን ለማምረቻነት እንደሚያገለግል አስታወቀዋል። የጌጣጌጦቹን በብርና በወርቅ ለመሥራት የሚሰራበት ማሽን ለመግዛት ሂደት ላይ መሆኑን ይገልጻሉ። አሁን ላይ ማዕድናቱን በመቅረጽ የአንገት ሀብል ፣ የእጅ አምባር እና የጆሮ ጉትቻ እና የመሳሰሉ በርካታ ጌጣጌጦች እየተሠሩ መሆኑን ያመላክታሉ። በተጨማሪም ከወርቅ እና ከብር ጋር የተለበጠ የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኙ የሚችሉ የተለያዩ ዓይነት የጌጣጌጥ ምርቶች እንደሚያመርትም አብራርተዋል።

‹‹የከበሩ ማዕድናት ላይ የሚሰሩት ሥራዎች እያሳደገን በተለያየ መልኩ በመሥራት ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውሉ እያደረግን ነው›› የሚሉት ተወካይ ዳይሬክተሩ፤ ኢትዮጵያ በርካታ ያልታወቁ ማዕድናት ያሏት ሲሆን፤ ኦፓል ደግሞ በጣም ረጅም ዓመት ያልቆየ በቅርብ እየታወቀ ያለ ነው። በመሆኑም ኦፓል በጥሬና እሴት ተጨምሮበት የሚሸጥበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ። ‹‹ የከበሩ ማዕድናት በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥም ያላቸው ድርሻ ውስን ስለሆነ ማዕድናቱን በማስተዋወቅ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከፍ ለማድረግ ጭምር እየተሠራ ነው›› ብለዋል።

ማዕድናቱ የውጭ ምንዛሪን ከፍ እንዲል እሴት መጨመርና ዲጂታል ገበያን መጠቀም አማራጭ ማድረጉን ተናግረዋል። አሁን ላይ የከበሩ ማዕድናት መሸጫ ሱቆች በማደራጀት እና በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ሥራ ድርጅት እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ የውጭ ተርሚናል ላይ እንዲኖር ማድረግ የከበሩ ማዕድናት ለሽያጭ እያቀረቡ መሆኑን አመላክተዋል።

በተጨማሪም ዲጂታል ገበያ በመጠቀምም ሆነ እሴት በመጨመር ማዕድናቱን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው። የከበሩ ማዕድናት በዲጂታል ገበያ ለመሸጥ በዳሸን ባንክ፣ በኢግል ላይን እና በማስተር ካርድ በዓለም ገበያ ተወዳደሮ ለመሸጥ የሚያስችለው ዝግጅቱ ተጠናቅቋል።

የከበሩ ማዕድናት በማስተዋወቅ በሀገሪቱ እድገት ውስጥ የበኩላቸው ድርሻ እንዲጫወቱ ተጨባጭ የሆኑ ሥራዎችን እየተሠሩ ነው ያሉት አሕመድ አባጊሶ፤ ይህን ሥራ የበለጠ እያጠናከሩ ማስቀጠል እንደሚያስፈልግም ይገልጻሉ። ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ በዓለም ላይ ዘመናዊ የሆኑ የከበሩ ማዕድናት ከወርቅና ከብር ጋር ማራኪ በሆነ መልኩ መሥራት የሚያስችሉ የተለያዩ ማቴሪያሎችን እና ጌጣጌጦች ለመግዛት በዝግጅት ላይ እንደሆኑም አክለው ገልጸዋል። ‹‹የዓለም ሀገራት ተሞክሮን ስንመለከት በከበሩ ማዕድናት የሚታወቁ እንደ ህንድ፣ ቱርክ የመሳሰሉ ሀገራት በዘርፉ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል። በመሆኑን እነዚህ ማቴሪያሎች ከእነዚህ ሀገራት በማስመጣት ማዕድናቱ ገበያ በማቅረብ ተወዳዳሪ መሆን ይቻላል›› ሲሉ አስረድተዋል።

ኮርፖሬሽኑ ማዕድናቱን በዘርፍ ከተሰማሩ አነስተኛ አምራቾች የሚወስድ ሲሆን፤ ከአራት ወራት በፊት የከበሩ ማዕድናት በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ 34 የሚሆኑ አነስተኛ አምራቾችን ማህበራትን ስልጠና መስጠቱን ተናግረዋል። ስልጠናውም ማዕድናቱን እንዴት ተቀነባብረው ወደ ገበያ በመቀየር እንደሚችሉና ማዘዋወር የሚቻልበት ሁኔታ ላይ ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል። ከስልጠናው በኋላ ማህበራቱ የሚሳተፉበትን የማዕድን ዓይነት በመለየት፤ በኮርፖሬሽኑ በጋር መሥራት የሚችሉበት ሥርዓትም መዘርጋቱን አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ላይ ማዕድናቱ ከተለያየ የኢትዮጵያ አካባቢ (ከትግራይ፣ ከአማራ፣ ከኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉልና ጋምቤላ ክልል ይመጣሉ። ኦፓል በስፋት በሚመረትበት በአማራ ክልል በወሎ ደላንታ አካባቢ ሲሆን፤ ኦፓል በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ማህበራትን በስፋት በማስልጠን ሕጋዊ በሆነ የማዘዋወሪያ ፈቃድ ማዕድኑን ለድርጅቱ እንዲሸጡ እየተደረገ ነው። ኮርፖሬሽኑ ማዕድናት ሲገዛ ሕጋዊ መስመር በተከተለ መልኩ የሚሰሩ ማህበራት ጋር ስለሚሰራ በማዕድን ላይ የሚነሳው ሕገ ወጥነት በመከላከል ሕጋዊ ሥርዓትን ተከትለው የሚሰሩ ማህበራት እንዲስፋፉ እንደሚያደርግ አመላክተዋል።

ይህም ሕገ ወጥ የማዕድን ሽያጭና ዝውውር በማስቀረት ሕጋዊ መስመር የተከተለ አሠራር እንዲኖር ያደርጋል። በተጨማሪም ባልተገባ መልኩ ወደ ውጭ ይወጣ የነበረው ማዕድን ማስቀረት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

ኮርፖሬሽኑ በዲጂታል ገበያ አማካይነት ማዕድናቱን በተለያዩ መሸጫ ሱቆች እና በዲጂታል ገበያ ለሀገር ውስጥ ሆነ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ መሆኑን የሚገልጹት አቶ አሕመድ አባጊሳ፤ በተለይ በዲጂታል ገበያ ሀገሪቷ ያሉትን ማዕድናት በዓለም ገበያ በማስተዋወቅ ማዕድናት እንዲሸጡ በማድረግ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪም እንዲጨምር የሚደረግ መሆኑ ያመላክታሉ። በዚህም ሀገሪቱም ከዘርፉ ማግኘት የሚገባት የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ አስታውቋል።

የከበሩ ማዕድናት እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ በማቅረብ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት አቶ አሕመድ አባጊሳ፤ እሴት በመጨመር ረገድ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ትልቅ ሥራ የሚጠይቅ እንደሆነ ይገልጻሉ። ሆኖም ግን አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችን በመግዛት እሴት በመጨመር ከተሠራ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚቻልበት ሥርዓት እንዲኖር ያስችላል ሲሉ አስገንዝበዋል።

‹‹አሁን ላይ በከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ዙሪያ እየተሠራ ያለው ሥራ ማዕድኑ በኢኮኖሚ ያለውን ሚና እየተወጣ ነው የሚባል ባይሆንም ፤ በሂደት እያደገ ያለ መሆኑ ያሳያል›› ያሉት ተወካይ ዳይሬክተሩ፤ እሴት ጭመራ ላይ ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች ስላሉ በሚፈለገው ልክ ለመሥራት ብዙ ጥረቶችን እንደሚደረግ አመላክተዋል።

‹‹ማዕድን የሀገራችንን ብልጽግና ከሚረጋገጥባቸው የኢኮኖሚ ምሰሶች አንዱ ሆኖ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ነው›› ያሉት ተወካይ ዳይሬክተሩ፤ በባለፈው ጥቅምት ወር በማዕድን ሚኒስቴር የተዘጋጀው የማዕድን ኤክስፖ ማዕድናት በዓለም እንዲተዋወቁ ያስችል እንደሆነ አንስተዋል። በተጨማሪም ማዕድን ሀገሪቷ ኢኮኖሚ ውስጥ ሊኖረው የሚችለው ድርሻ እንዲወጣ፣ ሕገ ወጥነት ለማስቀረት፣ ጥራት ያለው የማዕድን ሥራ እንዲሠራ፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ ውጤታማ ሥራ እንዲሠራ ዓይን መክፈቻ እንደነበር አስገንዘበዋል።

ኮርፖሬሽኑም በኤክስፖ ተሳታፊ እንደነበር አስታወሰው፤ በማዕድን በሀገሪቱ እድገት ውስጥ የበኩል ድርሻ እንዲወጣ ሰፊ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ያመላክተዋል። በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ውጤት እየተመዘገበ እንደሆነ ገልጸዋል።

የማዕድን ፍለጋውም ሆነ የማምረት ሥራው ሀገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚካሄድ በመሆናቸው የሚያጋጥሙ የተለያዩ ተግዳሮቶች መኖራቸው የጠቀሱት ተወካይ ዳይሬክተሩ፤ አሁን ላይ ከሰላምና ጸጥታ ጋር ተያይዘው የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች በሂደት እየተፈቱና እየተስተካከሉ የመጡበት ሁኔታ ስላለ ወደፊት ለማዕድን ሥራው አጋዥ የሆኑ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በቀጣይም ኢትዮጵያ ያላት የማዕድን ሀብቶች እና ሌሎች ሀብቶች ለማውጣትና ለመጠቀም ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ከዘርፉ ሀገሪቱ እንድትጠቀም እየተደረጉ ያለው ጥረቶች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ሲሉ አቶ አሕመድ አባጊሳ ሃሳባቸው አጠቃለዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ከጉርምስና እስከ ጉልምስና

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

አዲስ የገዛሁት ጫማ አቧራ ቅሞ ሳየው መሀረቤን ከኪሴ መኸርርጨ አበስ አደረኩት። ወደእሷና ወደእናቴ ስሄድ ተሽቀርቅሬ ነው። እናቴ ፊት ጎስቋላ እሷ ፊት መሀይምና የማይረባ መምሰል አልፈልግም። በቸምቸሞ ጥቁር ጸጉሬ መሀል ያገጠጡ ያለጊዜያቸው የበቀሉ ሽበቶች በማያውቁኝ ሰዎች ፊት አንቱታን ቸረውኛል። በልጅነቷ የምታውቀው ወዜ የለም። ጊዜ አቂሞብኝ ነው መሰል ያለእድሜዬ አገርጅፎኛል። አሁን ማን የልጅነት ፍቅረኛውን የሚጠብቅ ጎልማሳ ብሎ ያስበኛል?

### ጉርምስና...

ልጅነቴ አልቆ እንዴት ከአፍላነት እንደወደኩ አላውቀውም። ከስሬ የማጠፋ ከጥላዬ የተካከለች አንዲት ሴት እንደአንገቴ ዶቃ አብራኝ ተሰልፋ እንደነበር ይሄን አስታውሳለው። ከአንዲት እኔን መሳይ ነፍስ በቀር ትዝ የሚለኝ አንዳች የለም። ከእናቴ ጉያ ስሸሽ ማረፊያዬ እሷና ቀሚሷ ናቸው። ባልና ሚስት ሳንሆን የተጫወትነው እቃቃ የለም። ማንም የሚያውቀን እኔ ለእሷ ባል እሷ ለእኔ ሚስት ሆነን ስንጫወት ነው። የሌላ ሴት ባል ሆኜ በተጫወትኩባቸው የእቃቃ ዘመኖቼ አልቅሳ ባሏ ያደረገችኝን ልጅነቴን ሳስታውስና የሌላ እኩያዬ ሚስት ሆና ተደባድቤ ሚስቴ ያደረኩበትን የልጅነት ዘመኔን ሳስብ የማያባራ ሳቅ ይከጅለኛል።

እኩል ነው የጎረመስነው። ልጅነታችንን እስከጨረስንበት እስከ ቅርብ ዓመት ድረስ በቁመት እኩል፣ በሃሳብ እኩል ነበርን። ምኞታችን ራሱ የተወራረሰ ነው። በአንድ አእምሮና ልብ ወንድና ሴት የሆንን እንጂ በሁለት አእምሮና ልብ የምናስብ አንመስልም ነበር። ሰው እንዴት በሃሳብ እኩያ ይሆናል? በምኞት መቀራረብ እንጂ መመሳሰል በማን ላይ ደርሶ ያውቃል? በእድሜ እና በቁመት ይሁን በሃሳብ እኩያ መሆን ለማን ተችሏል? እኔና እሷን ሳስብ ከመደነቂያዬ አንዱ ይሄ ነው። በማላውቀው እና ተመልሶ እንዲመጣ በማልመኘው የሆነ ጠዋት ላይ ከእንቅልፌ ስነቃ ሌላ ሆኜ ነቃሁ። አድጌና ዘልጌ በእድሜ የሚበልጡኝን ሁለት ታላላቅ ወንድምና እህቶቼን በቁመት በልጬ፣ ከአባቴ አነስ ከተቀሩ ቤተሰቦቼ ከፍ ብዬ ራሴን በእንግድነት አገኘሁት። ያሳሰበኝ ማደጌ አልነበረም ከእንግዲህ እንደማታቅፈኝ ማመኔ ነበር። እኩያ እያለን ያለ ምንም መቸገር ነበር የማቅፋትና የምታቅፈኝ። እኔ ላይ ፊጥጥ እንደማለት የሚቀናት አንዳች የለም።

መጀመሪያ ስታየኝ የተሰማትን ስሜትና የሆነችውን መሆን መቼም አልዘነጋውም። አስታውሳለው ያን ቀን ረፋድ እንደ ሁልጊዜዋ አያቷ ጋ ልንሄድ (የአያቷ ሰፈር ከሰፈራችን በልጅ እርምጃ የ7 ደቂቃ ሰፈር ነው። ጠዋት ጠዋት እንደ ቤተክርስቲያን ገረገራ የአያቷን ቤት የመሳለም ግዴታ ጥላብኛለች። አያቷ ጋ ሳትሄድ እና እታባዬ ብላ ጉንጭዋን ሳታስም ቀን የላትም) በእኛና በነሱ ቤት መካከል ባለው የዛፍ ጥላ ስር ተቀምጣ፣ አንድ የእናቷን አንድ የእህቷን የተለያዩ ጫማዎች ተጫምታ የምንጫወትበትን እቃዎች ስታሰናዳ ነበር ድንገት ያየችኝ። እኔ አልመስል ብያት ለረጅም ሰዓት ስታስተውለኝ እና ከሆነ ሰው ጋር የተመሳሰልኩባት መስሏት ለማመን ስትቸገር አስታውሳለሁ። የምታውቀው እኔና የማታውቀው የሆነ ሰው ተቀይጠንባት ማነህ ምንድነህ ሳትለኝ ሕይወት ቀጠለ።

እጹብ የምትገርም የሕይወት ዛፍ ናት። ሞት ያለባት እጸበለስ ብትሆን እንኳን በድፍረት ቀንጥሻት የሞት ሞትን ልሞትባት ወደኋላ የማልላት ታሪኬ ናት። በሕይወቴ ደምቀው ከተሳሉት ዋናዋን ናት። ወደእኔ ስትመጣ በተንሻፈፈ ታሪክ ነው..በወጉ ለብሳ አንድም ቀን አይቻት አላውቅም። ልብስ ስትለብስ የሆነ ቦታ ላይ ትሳሳታለች። ብዙ ጊዜ እጅጌውን አንገቷ ውስጥ አስገብታ የተለየች ፍጥረት ሆና፣ የቀሚሷን ፊትና ኋላ አዙራ፣ በአንድ የጆሮ ጉትቻ አሊያም በማይመሳሰሉ ጌጦች ልጅነቷን የቋጨች ናት። በማይመሳሰሉ ጫማዎች፣ በተዘባረቁ የጆሮ ጌጦች ሴት የሆነች ናት። ምንም የማይመስላት..ምንም ቢመስላትም ከቅጽበት የማትርቅ ጅግኒት። ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ናት..እሷን እና እሷን መሳይ።

ከዛን ቀን ጀምሮ እኔን ለማቀፍ የምታደርገው ትንቅንቅ መዝናኛዬ ሆነ። ምነው ባላደኩ የሚለው የዘወትር ጸሎቴ ግን ከአፌ ላይ የሚያብሰው አልተገኘም። በእኔ ድንገተኛ መዝለግ ወዳጅነታችንን እየሸረሸረ ብዙ ጊዜ ራሴን ብቻዬን አገኘው ጀመር። ከዛ ማደግ በኋላ ጥቂት ዓመታት ተቆጠሩ። በሃሳብ ባንራራቅም በቁመት ሳትደርስብኝ ርቄያት ሄድኩ። በሁለት ወር እንደምትበልጠኝ ሰምቻለሁ..ግን ምናችንም እኩያ አይመስልም።

### የሆነ ቀን ጠፋች

ቆይቼ ስሰማ አጎቷ ጋ ስዊድን መሄዷን ሰማሁ። በየት በኩል እንደሄደች ግራ ገባኝ። በ24 ሰዓት ውስጥ አብረን የማንሆነው ለመጸዳጃ ቤትና ለሻወር ቤት አንዳንድ ጊዜም ለመኝታ ነው። እኚህንም ብዙ ጊዜ አብረን አድርገናቸዋል። ለዚህ የሚያበቃ መራራቅ በመካከላችን መች ተፈጠረና ራቀችኝ! ሳላይና ሳልሰማ በምን ቀዳዳ እንደሾለከች ባስብ ራቀኝ። እዚህ ላይ ራሴን ብዙ ጠየኩ.. ዓመታት በቅጽበት ሲደበዝዝ፣ ዘመን በአሁን ሲዋጥ ጊዜን «እናትክን» አልኩት። ናፍቆት በነበር ሲቀር፣ ትዝታ በመሄድ ሲሻር ዘመንን አቄምኩበት። ስንት ነገር አውግታኝ የለ ምናለ አንድ ጊዜ እፈልገሃለሁ ብላ እቃቃ የምንጫወትበት ጥላ ስር ቆማ ድንገት ስማኝ ቢሆን..ባልና ሚስት ስንጫወት አሳባ ፍቅሯን ብትነግረኝ ስል ብዙ አሰብኩ። ፍቅር እየሱስን የሚመስለው ተጀምሮ ሲያበቃ እንጂ ተጀምሮ ሲቆም አይደለም። ያላለቀ ፍቅር የገሀነም ዙሪያውን ነው።

እያሰብኳት ወደነገ በረርኩ። በጉርምስናዬ ላይ ብዙ ዓመታት ተጨምረው ወጣትነት አፋፍ ላይ ደረስኩ። እሷ የሌለችበት እኔ፣ ጥላዋ ያልደረሰበት ወጣትነት እጅግ ፈታኙ ጊዜዬ ነበር። ራሴው ለራሴ ከበደኝ። ከአዲሱ ማንነቴ ጋር ለመላመድ እጅግ ከብዶኝ ነበር። ከቤታችን ስወጣ እና ዓይኔን ወደቤታቸው ስሰድ በቁመት ከሚበልጣት ጆግ ውስጥ ውሀ እየጨለፈች ፊቷን ስታብስ የማውቀው ታሪክ እና ባልና ሚስት ሆነን የተጫወትንበት የጥላው ዛፍ ልቤ ውስጥ እሷን ማስታወሻ ሀውልት ሆነው በስሟ ቆመዋል። የልጅነታችን አድባሮች አሁን የሉም..ቤታቸው ፈርሶ አዲስ በተሠራ ሕንፃ ታሪኬ ድምጥማጡ ጠፍቷል። የጥላው ዛፍም ቦታው ላይ የለም። እንደነበር የሚቀጥል የለም ስል የምፈራው ይሄን እኮ ነው! እኔና እሷስ መች እንደነበርን ቀጠልን?

ቤተሰቦቿ ግቢያቸውን ለአንድ ድርጅት አከራይተው ከእኛ መንደር ፈቀቅ ብለዋል። ሕንፃው ሲሰራ ያን ዘወትር ማለዳ አብሯት የማየውን ቀይ ጆግ ስንት ታሪክ እንዳልጣፈ ቆሻሻ ገንዳ ላይ ሳየው ታሪኬን አውጥተው የጣሉት ነበር የመሰለኝ። ማታ ማንም ሳያየኝ ከቆሻሻ ገንዳው ላይ አንስቼ ከቤት ስወጣ ፊት ለፊት እንዳየው አድርጌ እንደ ሰንደቅ አላማ ከቤታችን ጣሪያ ላይ ከአንድ ከፍ አርጌ ሰቀልኩት። ከመጥፋት ግማሽ ትዝታዬንና ግማሽ ነፍሷን የታደኳቸው ይመስለኛል..

በአንድ ሰው የናፍቆት ሸለቆ ውስጥ ወድቆ ወደነገ ለመሄድ መቸገር ቅጣት ነው እላለሁ። በዚህም ሰው በመሆን ውስጥ መቅደም ያለበት ቀዳሚው ተማጽኖ ወደነገ ከማያሻግር እርባና ቢስ ሰውና ፍቅር ጠብቀኝ የሚል ይሆናል። በሰው ነፍስ ላይ የፈጣሪ ዱላ እንዲህ ያለው ቅጣት እንደሆነ ማንም አልነገረኝም። የማትመጣን አንዲት ነፍስ መጠበቅ፣ ለማይደርሱበት ለራቀ ታሪክ መንጠራራት ከዱብዳ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

ጊዜ ከትዝታዋ ሳያፋታኝ ጉልምስና እንባ ላይ አሳረፈኝ። ራሴ ሁለት ዓይነት ፀጉር ወለደ። አላገባሁም..ፍቅረኛ የምትሆን ጉብልም አልከጀልኩ። ያቺን የጠዋት ጀምበር እየሞኩ በሄደችበት መንገድ መመለሻዋን አስተውላለሁ። የሆነ ጠዋት ትዝታዬን ከሰወረብኝ ሕንጻ ላይ ዓይኔን ተክዬ ከእናቴ በኩል መምጣቷን ሰማሁ። አንዳንድ ቅጽበቶች አሉ ምንም እንዳንናገር የነፍሳችንን አፍ አድብነው በዝምታ የሚለጉሙ.. አንዳንድ ቀናቶች አሉ ከወሰዱብን አልቀው ሊሰጡን በትካዜያችን ሰሞን ከወደቅንበት የሚመጡ። እኔም ቅዝዝ አልኩ..መቼም ከማልደግመው ደስታዬ ጋር።

### ሳያት ልሄድ ነው..

አዲስ የገዛሁት ጫማ አቧራ ቅሞ ሳየው መሀረቤን ከኪሴ መኸርርጨ አበስ አደረኩት። ወደእሷና ወደእናቴ ስሄድ ተሽቀርቅሬ ነው። እናቴ ፊት ጎስቋላ እሷ ፊት መሀይምና የማይረባ መምሰል አልፈልግም። ግን ለምንድነው የምሄደው?

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ ናዚ ጀርመንን ያሸነፈችበትን የድል በዓል እያከበረች ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ በትናንትናው ዕለት ከ79 ዓመት በፊት ሶቪየት ህብረት የናዚ ጀርመን ወራሪ ኃይልን ያሸነፈችበትን የድል በዓል እያከበረች ነው።

ሶቪየት ህብረት ከፈራረሰች ከስምንት ዓመት በኋላ ወደ ስልጣን የመጡት ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን በቀዩ አደባባይ በሚካሄደው በዓል ላይ ንግግር ያደርጋሉ ተብሏል።

ሞስኮ ከዩክሬኑ ጦርነት በኋላ አነስ ያለም ቢሆን ወታደራዊ ትርኢት እንደምታሳይ ነው የተነገረው።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ ጀርመን እና የፋሽስት ጣሊያን ኃይልን ለማሸነፍ ከተባበሯት ሀገራት ጋር ግንኙነቷ ይበልጥ በሻከረበት ወቅት የሚከበረው የድል በዓል ለሩሲያውያን ትልቅ ስፍራ አለው።

“አባት ሀገራቸውን ለመጠበቅ መስዋዕትነት ለከፈሉት ሁሉ ትልቅ ክብር አለኝ” ለሚሉት ለፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲንም የበዓሉ ትርጉም ከፍ ያለ ነው።

አባታቸው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ ጀርመን ኃይልን መዋጋታቸውንና ጦርነቱ ያስከተለውን ጠባሳ ደጋግመው የሚያነሱት ፑቲን፥ ምዕራባውያን ሶቪየት ህብረት የሂትለርን ጦር በማሸነፉ ረገድ የነበራትን ድርሻ ዘንግተዋል ሲሉ ይወቅሳሉ።

የ71 ዓመቱ ፕሬዚዳንት ከትናንት በስቲያ ለአምስተኛ የስልጣን ዘመን ቃለ መሃላ ሲፈጽሙም የዩክሬኑ ጦርነት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የሶቪየት ህብረትን ብርታት ካለመረዳት የመነጨ ነው ብለዋል።

የአሜሪካ መራሹ የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) መስፋፋትንም ከናዚ ጀርመን ፍላጎት ጋር እንደሚያመሳስሉት አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

ዩክሬንና ምዕራባውያን አጋሮቿ ግን ሉዓላዊ ሀገር በመውረር መሬት የመያዝ “ያረጀ የንጉሳዊ አገዛዝ” እየተከተሉ ያሉት ፑቲን ናቸው በማለት ይወቅሳሉ።

የዩክሬንን ከ18 በመቶ በላይ ግዛት በቁጥጥሯ ስር ያስገባችው ሞስኮ በበኩሏ ጦርነቱ ከኬቭ ጋር ሳይሆን አይዞሽ ከሚሏት “የናዚ አስተሳሰብ አራማጅ” ምዕራባውያን ሀገራት ጋር እንደሆነ ትገልጻለች።

በቁጥጥር ስር ያዋለቻቸው የዩክሬን መሬቶችም ከዓመታት በፊት የታላቋ ሩሲያ አካል እንደነበሩና በመጥቀስ ወቀሳውን ውድቅ ታደርጋለች።

ዛሬ እያከበረችው ያለውን የድል በዓልም ብርታቷን ለዓለም ለማሳየት ትጠቀምበታለች።



ሶቪየት ህብረት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከ27 ሚሊየን በላይ ዜጎቿን ማጣቷ ይነገራል።

ጀርመን፣ ጣሊያን እና ጃፓን “አክሲስ ፓወር” በሚል ዓለምን በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ “ከተባበሩት ኃይሎች” አሜሪካ፣ ሶቪየት ህብረት፣ ብሪታንያ እና ፈረንሳይ ጋር ያደረጉት ጦርነት በርካታ ሀገራት የተሳተፉበትና ከወቅቱ የዓለም ሕዝብ 3 በመቶው ያለቀበት ነው።

በዩክሬን ምክንያት ሶስተኛው የዓለም ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ስጋቱ ባየለበት በዚህ ወቅት ሩሲያ ታክቲካል የኒዩክሌር ጦር መሳሪያዎች ሙከራ እንዲጀምር አዛለች።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አብረዋት የተሰለፉት ሀገራት አሁን ዋነኛ የደህንነት ስጋት እንደሆኑባት ገልጻለች።

አሜሪካ፣ ብሪታንያ እና ፈረንሳይ ለዩክሬን ከጦር መሳሪያ እስከ ወታደር በመላክ ኬቭን ከሞስኮ ጋር ሃይላቸውን የሚፈታተሹባት የጦር ሜዳ ካደረጓት ከሁለት ዓመት በላይ ተቆጥሯል።

## አሜሪካ ለእስራኤል በሰጠቻቸው ቦምቦች ንጹሃን ዜጎች መገደላቸውን አመነች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ለፍልስጤም ነፃነት እታገላለሁ የሚለው ሐማስ ባሳለፍነው ጥቅምት ወር በእስራኤል ላይ ድንገተኛ ጥቃት ማድረሱን ተከትሎ ነበር ጦርነት የተቀሰቀሰው።

እስራኤል በሐማስ ታጣቂዎች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ባለችው መልሶ ማጥቃት ከ34 ሺህ በላይ ፍልስጤማዊያን ተገድለዋል።

ፕሬዚዳንት ባይደን ከሲኤንኤን ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ " ለእስራኤል በሰጠነው ቦምብ ንጹሃን ተገድለዋል" ብለዋል።

"ወደ እስራኤል ቦምብ አንልክም" ያሉት ፕሬዚዳንቱ እስራኤል ወደ ራፋህ ጦሯን እንዳትልክ እና ንጹሃንን እንዳትጎዳ ለጠቅላይ ሚንስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ መናገራቸውንም ጠቅሰዋል።

እስራኤል ጦሯን በርካታ ስደተኞች ወደ ተጠለሉበት ራፋህ ከላከች ተጨማሪ ርምጃዎች ሊወሰድ ይችላል ሲሉም ፕሬዚዳንቱ በቃለ መጠይቃቸው ላይ ተናግረዋል።

ይሁንና የእስራኤል ጠቅላይ ሚንስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ የሐማስ ታጣቂዎች በራፋህ እንደሚገኙ እና እነሱን ለመደምሰስ ጦራቸው ወደ ራፋህ መግባቱን ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚንስትሩ አክለውም ወደ ራፋህ እንዳንገባ የሚከለክለን አካል የለም ያሉ ሲሆን ስለ አሜሪካ አዲስ ውሳኔ እስካሁን በይፋ ከመናገር ተቆጥበዋል።

በተመድ የእስራኤል አምባሳደር ጊላድ ኤርዳን የአሜሪካ ውሳኔ የሚያበሳጭ ነው ያሉ ሲሆን ዋሽንግተን ለእስራኤል የምትሰጠውን ድጋፍ ማቆም የለባትም ብለዋል።

ከአሜሪካ በተጨማሪም ካናዳ እና ሌሎችም የአውሮፓ ሀገራት ለእስራኤል የጦር መሳሪያ እንዳይሸጥ እገዳ ጥለዋል።

እስራኤል እና ሐማስ የተኩስ አቁም ለማድረግ፣ ታጋቾችን



ለመልቀቅ እና ሌሎችንም ጉዳዮች ለመመለስ በሚል የሰላም ስምምነት ለመፈራረም የተስማሙ ቢሆንም አዲሱ የራፋህ ጥቃት ስምምነቱ እንዲፈርስ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ተሰግቷል አልአይን ኒውስ ዘግቧል።

# ነፃ ሃሳብ

ከ ገጽ 5 የዞረ

## ሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ...

አካባቢ እንደወረርሽኝ እየጨመረ የመጣውን የሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ እና ተጓዳኝ ችግሮች ማጥፋት ባንችል እንኳን በከፍተኛ ቁጥር ለማዳፈን ያስችለናል። በዚሁ መድረክ ከሀገር ውስጥ ወደየ ስፖርት ማዕከሎች እየሄዱ ቢጠይቁ ወይም ሌሎችም ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ቢመቻች እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ምስክርነት ሊሰጡ ይችላሉ። ቀድሞ ለዓመታት መድኃኒት ሲወስዱ የነበሩ ክብደት በመቀነስ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን የኑሮ ዘይቤ በማድረግ እና አመጋገብን በማስተካከል (በተለይ ጤናማ ያልሆነ የአንጀት ውስጥ ተህዋስያን አለመመጣጠን ችግር/ Gut microbiota dysbiosis) የሚያስከትሉትን ምግቦች በመተው፣ ለዓመታት ከመድኃኒት ነፃ የሆኑ ሰዎችን ማግኘት እና ከልምዳቸው ብዙ መማር ይቻላል። ሕዝባችን ከዶክተር ከሚሰማ ልምዳቸውን ከሚያካፍሉ ሰዎች የበለጠ ማወቅ ይፈልጋል። በውጭ ሀገር ካሉት ደግሞ ከኢንተርኔት ላይ የብዙ ሰዎችን ልምድ ማንበብ እና ለሕዝቡ ማካፈል ይቻላል። እጅግ ብዙ ሰዎች ለራሳቸው ሐኪም ሆነዋል። ይህ እንደሚቻል ብዙ የሕክምና ባለሙያዎች ያውቃሉ።

ታዲያ መቼ ነው ሁለተኛውን ዓይነት የስኳር በሽታ ማዳፈን እንደሚችል በይፋ ለመናገር የምንደፍረው? ለዓመታት መድኃኒት ላይ ጥገኛ የነበሩ ከመድኃኒት ነፃ ሆነው የሕይወት ዘይቤያቸውን የቀየሩ ሕያው ምስክሮች እጅግ ብዙ እያሉን? ያው እንደብዙው ነገር ፈረንጅ መጥቶ እስኪነግረን መጠበቅ አለብን? እነሱ እዚህ መጥተው ባይናገሩ ከሰሯቸው ምርምሮች በቂ መረጃ አግኝተናል። እኛም ልምዳችንን በምርምር አስደግፈን ብናወጣው ጤና ሚኒስቴር ሀገራዊ ንቅናቄ ለመፍጠር በፕሮግራም እንዲይዘው እና አጋሮችን እንዲያስተባብርበት ትልቅ መሳሪያ ይሆነዋል።

በስኳር ሕመም ሕክምና ስፔሻላይዝ ያደረጉና የብዙ ዓመት ልምዳቸውን (አንድ ሳይሆን ሶስት አራት ወይም ከዚያ በላይ) እንዲያካፍሉ ማድረግ ቀዳሚ ቢሆን ጥሩ ነው። የስኳር በሽታ ማህበር ልምድ ቢጠየቅ ብዙ የማናውቀው ልምድና ምክረ ሃሳብ ማግኘት ይቻል ይሆናል። መልዕክቱ ሳይንሳዊ መረጃዎችን እየመረመርን እና የሀገራችንን ልምድ በምርምር መልክ እያቀረብን ከዘመኑ ጋር መራመድ መቻል አለብን የሚል ነው። የዚህ ችግር ተጠቂዎች የሆኑ በሽታውን ለማዳፈን በራሳቸው ጊዜ ብዙ ነገሮችን ሲሞክሩ ማየት የተለመደ ነው። ይሁን እንጂ በባለሙያ (የሕክምና፣ የሥነ ምግብ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና የሥነ ልቦና) የተደገፈ ምክር እያገኙ ቢሆን ውጤቱ የሚባዛ ይሆናል። ሕዝብ ስለጤናው ጠያቂ እና ጤናውን ጠባቂ እንዲሆን በቂ ግንዛቤ ይኖረዋል።

የእኔ ስጋት (በውይይቱ ጊዜም እንደተጠቆመው) ሕዝባችን በዚህ መረጃ (በፕሮግራሙ ላይ ከቀረበው) ብቻ ተነሳስቶ ግብታዊ የሆነ ስህተት እንዳይፈፅም (መድኃኒት መውሰድ በአንድ ጊዜ እንዳያቆም) ነው። መሰል ክርክሮች ለሕዝብ ሳይሆን ጥናት ሰርቶ ቀድሞ እርስ በርስ ቢሆን መልካም ነበር (በጤና ጉዳይ ባለሙያዎቹን አንተ ምን ትላለህ? አንተ ምን ትላለህ? ብሎ መጠየቅ ሕዝብን ውዥንብር ላይ የሚከት ነው)። እንደዚያ ለማድረግ አሁንም አልረፈደም፤ አዲስ ጥናት ማካሄድ ባይቻል በብዙ ሀገሮች የተሰሩትን አሰባስቦ በዓመታዊ ጉባኤዎች ላይ በማቅረብ ብዙዎቹ ሐኪሞች ሃሳቡን እንዲገዙት እና ታካሚዎቻቸውን ሁሉንም የማዳፈኛ ዘዴዎች እንዲተገብሩ በአማራጭነት እንዲያቀርቡላቸው ማድረግ ይቻላል።

ስለዚህ የመጀመሪያው ሥራ መሆን ያለበት ሳይውል ሳያድር በሕክምና ባለሙያዎች ዘንድ ሃሳቡን የጋራ ማድረግ እና ሕዝቡ ከሚያምናቸው ባለሙያዎች በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ታካሚዎች መድኃኒት ከማቆማቸው በፊት በቅደም ተከተል ሊፈፅሟቸው የሚችሉትን ማሳወቅ ያስፈልጋል። ታካሚዎችም መድኃኒት ከማቆማችሁ በፊት እጃችሁ ላይ ባለው የግሉኮስ መለኪያ ማሽን ተማመኑ፤ ስኳር መቀነሻውን እየተገበርኩ ነው በሚል ስኳሩ ሳይቀንስ መድኃኒት ማቆሙ አደጋው የከፋ ይሆናል። ከአሁን በፊት የስኳር በሽታ ብቻ ሳይሆን ኤች አይ ቪን ጨምሮ በባህል ሕክምና እናድናለን፣ "መድኃኒት ወይም መንፈሳዊ ፈውስ (ፀበልን ጨምሮ) ምረጡ" በሚሉ ምክሮች ብዙ ሰው ተጎድቷል (ሁለቱም የእግዚአብሔር ሥራ ስለሆነ በተጓዳኝ ውሰዱ ቢሏቸው ባልከፋ ነበር)። ከመሰል ስህተት ለመዳን በቅድሚያ መድኃኒቱን እየወሰዱ ከመድኃኒቱ ነፃ ለመሆን የባለሙያ ምክረ ሃሳቦችን መተግበር እና የስኳር መጠንን በጥንቃቄ መከታተል ያስፈልጋል።

ርግጥ ነው ለሁለተኛው የስኳር በሽታ አባባሽ (Factors) የሆኑትን መተው ወይም ለበሽታው መቀነስ የሚያግዙትን መተግበር ስኳር በደም ውስጥ እንዳይበዛ ብቻ ሳይሆን ማዳፈን ያስችላል። ከሁሉ በፊት ሊተኮርበት የሚገባው ይህን ማሳካት (ማዳፈን) የሚችሉት ሁሉም የሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ ያለባቸው ላይሆኑ ይቻላሉ (ቢያንስ በእድሜ የገፉ ሰዎች፣ መንቀሳቀስ የማይችሉ አካል ጉዳተኞች፣ የአእምሮ ታማሚዎች፣ ከሁለተኛው ወደ አንደኛው አይነት የስኳር በሽታ "የተቀየሩ"፣ በአብዛኛው በዘር ለሁለተኛው የስኳር በሽታ እና ተጓዳኝ ለሆኑ በሽታዎች ተጋላጭ የሆኑ እና Autoimmune poly-endocrine syndrome ተጠቂ የሆኑ ሰዎች በጣም እንዳይብስ ማድረግ ይችሉ ይሆናል እንጂ እስከ ማዳፈን ላይሳካላቸው ይችላል)። በመጀመሪያው ሶስቱ የሚመደቡት ከፍተኛ የሰውነት ክብደት ያላቸው ከሆኑ በኦፕሬሽን (Bariatric surgery) ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ።

ስለሆነም ምክሩን ስንሰጥ ለይተን መሆን አለበት። እንደዚያ ስል የስኳር በሽታ ያለባቸውን እንደማሳነፍ ተደርጎ እንዳይወሰድብኝ። አዕምሮ ትልቅ ኃይል አለውና አንድ ሰው እችላለሁ ብሎ ከተነሳ ብዙ ነገር ይችላል። ህዋሳቶቻችን ንቁ አዕምሯችን ካገዛቸው እጅግ ብዙ ዓይነት በሽታዎችን መከላከል እና ማዳፈን ይቻላል። ሁሉም ነገር ያለው ህዋሳቶች ላይ ነው። ህዋሳቶቻችን ችግኞች ናቸው።

የሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ መነሻው ሰውነታችን (ህዋሳቶቻችን) ካርቦሃይድሬት የበዛባቸውን ምግቦች መጠቀም ሲያቅተው (ሳይፈልግ) እንደሆነ ይታወቃል። ለምን ለሚለው ብዙ መላምቶች ቢሰጡም በትክክል አይታወቅም። አንዳንዱ በዘር የሚወረስ ነው። እዚህ ጋ የሚታወቀው (ለሁሉም ባይሆንም) አጋላጭ የሆኑትና ሂደቱ ነው (ሰውነታችን ካርቦሃይድሬት መጠቀም የማይችለው) 1. በመጀመሪያ ባለመንቀሳቀሳችን (ጡንቻችን ስላልሰራ) ወደ ኃይል (ATP) መቀየር ሳይችል ሲቀር ወይም 2. ግላይኮጅን በሚባለው መልኩ መከማቸት ከሚችለው በላይ ሲሆንበት እና ከዚሁ ጋር በተያያዘ 3. ትርፍ የሆነው ካርቦሃይድሬት ወደ ስብነት መቀየር ሳይችል ሲቀር ነው። ካርቦሃይድሬት በቀዳሚነት ኃይል ሰጭ በመባል ቢታወቅም መከማችት ከሚችለው ወይም ለኃይል ምንጭነት መጠቀም ከምንችለው በላይ የሆነው ሁሉ ወደ ስብነት ይቀየራል።

እነዚህ ሶስት ሂደቶች በትክክል የሚከናወኑት በልጅነት እና በወጣትነት እድሜ ላይ እያለን፣ እድሜያችን ሲገፋም በቂ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በማድረግ ውፍረትን ስንከላከል እና አመጋገባችንን ስናስተካክል ወይም በዘር ተጋላጭ ካልሆንን ነው። እድሜያችን ከፍ እያለ ሲመጣ እንቅስቃሴ አለማድረጋችን ብቻ ሳይሆን ትርፍ የሆነውን ካርቦሃይድሬት ወደ ጮማነት የመቀየር ሂደቱ ይቀንሳል፤ ኢንሱሊን ለሚባለው ሆርሞን በአንዳንድ ሰዎች ላይ አልታዘዝ ይላል። በቀላል አማርኛ ህዋሳቶቻችን እራሳቸው ውፍረትን መከላከል ይጀምራሉ፤ ጡንቻችን ስለማይሰራ የለሙ የካርቦሃይድሬት ንጥረ ነገሮችን መቀበል ይቀንሳል። በሁሉም ሰው ላይ ባይሆንም ይህም (ህዋሳት ለኢንሱሊን በጎ ምላሽ አለመስጠት) የህዋሳት እርጅና አንዱ ምልክት ነው።

በተለይ ቀድሞ በሥራም ይሁን አቅዶ በቂ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያደርግ የነበረ ሰው ሁሉንም አቁሞ ቢሮ መቀመጥ ሲያበዛ፣ ሁልጊዜ ሊፍት ላይ ሲንጠለጠል፣ የመኪና ወዳጅ ሲሆን፣ በትንሽ መጠንም ቢሆን ጤናማ አይደለም የሚባለውን አልኮል ሲያዘወትር፣ እድሜ ከፍ ሲል፣ ህዋሳቶች ግሉኮስ መጠቀም ይቀንሳሉ። ምክንያቱም ከግሉኮስ የሚያመርቱትን ኃይል (ATP) እየተጠቀምንበት አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ ከእናት ከአባቱ ያልወረሰው ወይም ሲወለድ የቀነጨረ ሆኖ ጤናማ ያልሆነ የሰውነት ክብደት ሲጨምር፣ አእምሮው በሥራ ጫና ሲወጠር፣ በረጅም ጊዜ ሂደት ግሉኮስ ለአንጎል እና ለልብ በብዛት እንዲሄድ ይደረጋል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሥራ የሚበዛባቸው እነዚህ አካሎች ስለሆኑ ግሉኮስ ወደነሱ እየተላከ፣ ስትረስ እየጨመረ፣ ስትረስ ለሰውነት ብግነት (Inflammation) እያጋለጠ፣ ቶሎ ቶሎ የማይቀየሩት የጡንቻ ህዋሳት እየሟሸሹ ሲሄዱ፣ የስብ ክምችት በጉበት እና በቆሽት ላይ ይጨምራል። የቅርብ ጊዜ ጠንካራ ሳይንሳዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በየትኛውም መጠን ያለ አልኮል ጎጂ እንጂ ጠቃሚ አይደለም። አልኮል ከፍተኛ ካሎሪ ካላቸው ምግቦች የሚመደብ ስለሆነ የስኳር በሽታ አባባሽ ነው። የስኳር በሽታም አልኮልም ጉበት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ መሆናቸው ችግሩን "ከድጡ ወደ ማጡ" ሊያደርገው ይችላል።

በመሆኑም (ካርቦሃይድሬት መብላታችንን እስካልቀነስን ድረስ፣ ብንቀንስ እንኳን ሌሎች የምግብ ዓይነቶችንም አብዝተን ከወሰድን ወደ ግሉኮስ የሚቀየሩበት ሂደት ስላለ) በደም ውስጥ ያለው የስኳር መጠን እንዲጨምር ያደርገዋል። በትክክል ብንገነዘበው (በውይይቱም እንደተገለፀው) የስኳር መጠን መጨመር ህዋሳት እንደቀድሞው አለመሥራታቸው አንዱ ምልክት ነው። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ካላደረግን የጡንቻ ህዋሳት ስለማይሰሩ ኃይል (ATP) የሚሰጥ የላመ ምግብ (ግሉኮስ) መቀበላቸውን ይቀንሳሉ፤ ጉበትና ጡንቻ ውስጥ በግላይኮጅን መልክ መከማቸት ከሚችለው በላይ የሆነው ግሉኮስ ወደ ስብነት መቀየሩ ይቀንሳል፤ ከስብ የሚገኙት የኃይል ምንጮች (Ketone bodies) ይጨምራሉ (ይህም በጥቅሉ ሰውነታችን ግሉኮስን ለመጠቀም ለኢንሱሊን አልታዘዝ አለ ይባላል (Insulin resistance)። በርግጥም የጡንቻ ህዋሶች እንዳይሰሩ ያደረጋቸው ንቁ አእምሯችን ነው (ስንፍና)።

ሰውነታችን ያልተቃጠለ የካርቦሃይድሬት (ወደ ኃይል ምንጭነት ያልተቀየረ) ምግብን በግላይኮጅን መልክ መከማቸት የሚችለው እንደሰውነታችን ክብደት መጠን ከ300-500 ግራም ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ከምንበላው ጋር ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ነው። ሂደቱ እየሠራ ከሆነ እና ህዋሳቶች ለመደበኛ ሥራ ከሚያስፈልጋቸው (Basal metabolism) ውጭ የሆነው፣ በተጨማሪ የህዋሳት ሥራ (እንቅስቃሴ) ያልተቃጠለው በዋናነት ጉበት ውስጥ ወደ ስብነት ይቀየራል (Lipogenesis)፤ ስቡ በተለያየ የሰውነት ክፍል (ጉበትና ቆሽትን ጨምሮ) ይከማቻል።

ትንሽ ሰፋ ለማድረግ (ከይቅርታ ጋር) ካርቦሃይድሬት የሆኑ ምግቦች በኤንዛይሞች አማካኝነት በአብዛኛው ወደ ግሉኮስ ተቀይረው በደም ስር ይመጠጣሉ። ከዚያም ከረጅም ኬሚካላዊ ሂደት በኋላ በህዋሳቶች ውስጥ አሴታይል ኮ ኤንዛይም A (Acetyl CoA) ወደሚባለው ኬሚካል ይቀየራሉ። ቁልፉ ነገር እዚህ ደረጃ ከደረሰ በኋላ ነው። 1. ከተንቀሳቀስን ወደ ኃይል ምንጭነት (ATP) ይቀየራሉ (የበላነው ምግብ "ተቃጠለ" ይባላል)። 2. ካልተንቀሳቀስን እና ህዋሳቶች ለመቀበል ዝግጁ ከሆኑ (ለኢንሱሊን በጎ ምላሽ ከሰጡ) ወደ ስብነት ይቀየራሉ (እንወፍራለን)። 3. ካልተንቀሳቀስን እና ህዋሳቶች የተመረተውን Acetyl CoA ለመቀበል ዝግጁ ካልሆኑ ተጨማሪ ግሉኮስ ወደ Acetyl CoA አይቀየርም፤ እንዲያውም ህዋሳቶች የስብ ቅንጣቶችን መጠቀም ስለሚጀምሩ ፕሮፓዮኒል CoA (Propionyl-CoA) እና ሌሎችም የስብ ኬሚካሎች በህዋሳት ውስጥ ይበዛሉ። ይህ ደግሞ ግሉኮስ ወደ ህዋሳት እንዳይገባ ይከላከላል። 4. ግሉኮስ ደም ውስጥ እየበዛ ስለሆነ (Insulin resistance ወይም ለኢንሱሊን አለመታዘዝ ስላለ) እንዲቀንስ ለማድረግ የኢንሱሊን መመረት በከፍተኛ መጠን ይጨምራል (Hyperinsulinemia)። ኢንሱሊን የሚያመርቱ የቆሽት ህዋሳት (Beta cells) ደም ውስጥ ስኳር መብዛቱን ሲያሹቱ ኢንሱሊን በማምረት ሥራ ይበዛባቸዋል። ነገር ግን የጡንቻ ህዋሳቶች እየሠሩ ስላልሆነ (ለኢንሱሊን አልታዘዝ ስላሉ) የተወሰነው ግሉኮስ በስብ መልክ ጉበት ውስጥ ይከማቻል። የቀረው ግሉኮስ ሳይቀየር በደም ውስጥ ይከማቻል (ሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ ተፈጠረ ይባላል)።

የድምር ውጤቱ (ጮማ በጉበት ውስጥ መከማቸቱ የሚቀጥል ከሆነ) ችግሩን የሚያብስ ይሆናል፤ ምክንያቱም ተጨማሪ የስብ ቅንጣቶች ወደተለያዩ ህዋሳት ይለቀቃሉ፤ ኢንሱሊን ከምታመርተው ቆሽት ጭምር ስብ ይከማችና ኢንሱሊን ማምረት ያቅታታል። የሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ ምልክቶች መታየት ሲጀምሩ በደም ውስጥ ከፍተኛ ግሉኮስ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ኢንሱሊን ጭምር ይገኛል። በጊዜ ሂደት ኢንሱሊን የሚያመርቱ የቆሽት ህዋሳት በጮማ ክምችት እየደከሙ ሲመጡ የኢንሱሊን የመመረት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል (ከHyperinsulinemia ወደ Hypoinsulinemia)።

የኢንሱሊን የመመረት መጠን እየቀነሰ ሲመጣ በደም ውስጥ የሚከማቸው የግሉኮስ መጠን የበለጠ ይጨምራል። በዚህ ጊዜ ብዙ መጠን ያለው እና ዓይነቱም የበዛ የሁለተኛው ዓይነት የስኳር በሽታ መድኃኒት ቢወሰድ ውጤታማ አይሆንም። አንዱ አንዱን እያባሰ መመለስ ወደማይችልበት ደረጃ ያደርሳል ወይም አዙሪት ይፈጠራል/ጡዘቱ ይከርና ጉዳቱ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ይደርሳል። የቆሽት ህዋሳት በ0.5 ግራም ስብ ክምችት ከጥቅም ውጭ ሊሆኑና ኢንሱሊን ማምረት ከመቀነስ አልፈው ሊያቆሙ ይችላሉ። እዚህ ደረጃ ሲደርስ መድኃኒቱን ወደ ኢንሱሊን መቀየር ግድ ይሆናል። ታካሚውም የሁለተኛው ዓይነት ሳይሆን የአንደኛው ዓይነት የስኳር በሽታ ያለበት ተብሎ ይመደባል። ለዚያ ነው ብዙዎች ኪኒን ሲወስዱ ይቆዩና ወደ መርፌ (ኢንሱሊን) የሚቀየርላቸው። ይሄ ጥሩ ምልክት አይደለም።

በእንደዚህ ዓይነት መድረክ ፍንጭ እንጂ ማብራሪያ ለመስጠት አመች ስላልሆነ የቀረበውን አስተያየት አስመልክቶ (ሁለተኛውን ዓይነት የስኳር በሽታ ለማዳፈንም ሆነ ቀድሞ ለመከላከል) ሰዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ በሚለው ላይ ትንሽ ልበል። በቅድሚያ ስድስት ነገሮችን ለመፈፀም መዘጋጀት ያስፈልጋል።

1. የመጀመሪያውና ከሁሉም ቀዳሚው በቂና ዘላቂነት ያለው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ነው።
2. አመጋገብን ማስተካከልና የሚያብስብንን ምግብ ሁሉ ለይቶ መተው ነው።
3. እፅ ከሚባሉ (አልኮል፣ ትምባሆ በሲጋራ ወይ በሺሻ፣ ጫት፣ ሱስ አስያዥ መድኃኒት እና ሌሎች) ሁሉ መታቀብ ያስፈልጋል።
4. ስትረስን በሚቻለው ሁሉ መቀነስ (ሥነ ልቦናዊ እና አካላዊ ስትረስ ለረጅም ጊዜ እንዳይቆይ ማድረግ ሁለተኛው ዓይነት ስኳር በሽታ ጨምሮ ከብዙ ነገር መከላከል ያስችላል)።
5. በቂ የፀሐይ ብርሃን ማግኘት (እጅግ ብዙ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ሁለተኛው ዓይነት ስኳር በሽታን ጨምሮ ከቫይታሚን ዲ እጥረት ጋር እንደሚገናኙ ብዙ አዳዲስ መረጃዎች እየወጡ ነው)። ሳይታወቀን ለቀናት በቂ የፀሐይ ብርሃን ሳናገኝ እየቆየን ብዙዎቻችን (የቢሮ ሰዎች) ለቫይታሚን ዲ እጥረት የተጋለጥን ነው።
6. በቂ እንቅልፍ ማግኘት (አንዱ የስትረስ እና የደም ስኳር መጠን መቀነሻ መፍትሔ ስለሆነ)

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

## ነህሚያ-የበጎነት ተምሳሌት

ማህሌት አብዱል

ወይዘሮ ራሄል አባይነህ ትባላለች።የነህሚያ ኦቲዝም ሴንተር መስራችና ዳይሬክተር ነች። የተወለደችው በአባ ጅፋር ጅማ ከተማ ይሁን እንጂ ያደገችው፣ የተማረችውና ተድራ ሶስት ልጆቸ ያፈራችው እዚሁ አዲስ አበባ ነው።

በትዳሯም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቷ ደስተኛ መሆንዋን የምትገልጸው ራሄል፣ ሁለተኛ ልጇን እንደወለደች ግን ያልጠበቀችው፣ ይሆንብኛል ብላ ፈፅሞ ያልጠረጠረችውና በጊዜው አስደንጋጭ የሆነ ነገር እንዳጋጠማት ታስታውሳለች።ይኸውም ማርዬ እያለች እያቆላመጠች የምትጠራው ሁለተኛ ልጇ ከኦቲዝም (የአዕምሮ እድገት ውስንነት) ጋር መወለዱ ነው፡፡

ልጇ ኦቲዝም እንዳለበት ያወቀችበትን አጋጣሚ አስታውሳ ‹‹እኔ ልጄ ኦቲዝም እንዳለበት ያወቅሁት ሁለት ዓመት ከስምንት ወሩ ላይ ነው፣ ይሁንና ከአንድ ዓመቱ ጀምሮ ባህሪው ከሌሎች ልጆች የተለየ መሆኑ፣ መናገርና እንደልቡ መፅዳዳት ያለመቻሉ፣ በቂ እንቅልፍ የማይተኛና ራበኝ የማይል በመሆኑ ሁልጊዜም ጥያቄ ይፈጥርብኝ ነበር።በመሆኑም ችግሩን ለመረዳት ስል የተለያዩ የህክምና ተቋማት ሄጄያለሁ፣ ግን ደግሞ አንዳቸውም ችግሩን ቶሎ ሊያገኙለት አልቻሉም›› በማለት ታብራራለች።

‹‹አንድ ቀን ግን በአረብ ቻናል ተመሳሳይ ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ስመለከት የልጄ ችግር ኦቲዝም ሊሆን እንደሚችል ጠረጠርኩኝ፣ በጉዳዩም ላይ የምግባባውን ሐኪም / ዶክተር/ አማከርኩት፣ እሱ ግን ልጄ ኦቲዝም እንደሌለበት ሆኖም የበለጠ ርግጠኛ ለመሆን በዘርፉ ያጠና ባለሙያ ጋ ላከኝ፣ ሲመረመር ግን ልጄ ኦቲዝም እንዳለበት ተረጋገጠ›› ስትል ታክላለች።ስልጇ ሁኔታ ቀድማ ብትገነዘብም በሐኪሞች ምክንያት በመዘናጋቷና ለልጇ ቶሎ ድጋፍ ባለመድረጓ ዛሬም ድረስ በቁጭት የምታነሳው እንደሆነ ታነሳለች፣ በዚህ ረገድ ብዙ ወላጆች ተመሳሳይ ሁኔታ ሊያጋጥማቸው ስለሚችል የሕክምና ባለሙያዎች ከጊዜው ጋር የሚራመድ እውቀት ሊያጎለብቱና ከማህበረሰቡ ቀድመው ሊገኙ እንደሚገባ ትመክራለች።የጤና ባለሙያዎች በቂ ግንዛቤና ዝግጅቱ ከሌላቸው ጦሱ ለወላጆች እንደሆነ መገንዘቡ ጠቃሚ ነው ባይም ነች፡፡

ይህንን ተቋም ልትመሰረት የቻለችው ለልጇ የሚሆን ትምህርት ቤት በማጣቷና እንደእርሷ ብዙ እናቶች እየተቸገሩ እንደሚኖሩ በመገንዘቧ ነው።‹‹እኔም ሆንኩኝ በተመሳሳይ መልኩ ከኦቲዝም ጋር የተወለዱ ልጆች ያሏቸው ወላጆች ለእነሱ የሚሆን ትምህርት ቤት በማጣት ምክንያት ማህበረሰቡ የሚሰጠውን በጎ ያልሆነ አስተያየት ተቀብለን ቤት ውስጥ እንድንቀመጥ የተገደድንበትን ሁኔታ ለመቀበል ፍቃደኛ አልነበርኩም፣ እናም ልጄና ተመሳሳይ ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ሕይወት መታደግ እንዳለብኝ በማመኔ ነው›› በማለት ትገልፃለች።

ባደጉት ሀገራት ከኦቲዝም ጋር የተወለዱና ትልልቅ ደረጃ የደረሱ ሰዎች መኖራቸውን ጠቅሳ፣ ይህ ሊሆን የቻለው ግን ሀገራቱ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠታቸውና እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ሊያስተናግድ የሚችል ተቋም መስርተው በቂ ድጋፍ የሚያደርጉላቸው በመሆኑ ጭምር እንደሆነ ታስረዳለች።

‹‹እኛ አጠቃቀሙን አላወቅንም እንጂ በዓለም ላይ ከኦቲዝም ጋር የሚኖሩ ሰዎች በያዙት ነገር ውጤታማ ናቸው።እንደቢልጌት፣ አልበርት አንስታይን፣ ሞዛርት ያሉና ከራሳቸው አልፈው ለብዙዎች የተረፉ አነጋጋሪ ሰዎች ከኦቲዝም ጋር የተወለዱ ናቸው።እኛ ግን እነዚህን ሰዎች መጠቀም ያለመቻላችን እንደሀገር ኪሳራ ላይ ነን ብዬ አስባለሁ›› ስትልም ታብራራለች።በመሆኑም እነዚህን ልጆች ትምህርትና የተለያዩ ሕክምናዎች አግኝተው እንዲያድጉ በማድረግ ይዘው የመጡትን እውቀት ልንጠቀምበት ይገባል ስትል ትጠቁማለች።






ወይዘሮ ራሄል አባይነህ

ስለ ኦቲዝም የነበራት እውቀት እንዲህ እንደ አሁኑ አይሁን እንጂ ሊቃሉ አዲስ እንዳልነበረች፣ በተለይ ሌሎች ከሷ በፊት ተመሳሳይ ድርጅት የከፈቱ ሰዎች በመገናኛ ብዙሃን ስለበሽታው በሚያደርጉት ገለፃ የተወሰነ መረጃ ማግኘቷን ትገልፃለች።ይሁንና እቤቴ ይገባል ብላ ፈፅሞ ያልጠረጠረችው ጉዳይ ስለነበር እምብዛም ትኩረት ትሰጠው እንዳልነበር ትናገራለች።

ወይዘሮ ራሄል እንኳን ማህበረሰቡ ኦቲዝምና ተያያዥ ችግሮች ያሉባቸውን ሕፃናት፣ ከፈጣሪ ቁጣ ጋር የማያያዝና እንደተለየ ፍጡር የማየት ክፉ ባህል ቢኖርበትም እሷ በኖረችበት ገርጂ አካባቢ አብዛኛው ሰው የነቃና ስለጉዳዩ ግንዛቤ ያለው በመሆኑ እንዲህ ዓይነቱ ችግር እምብዛም እንዳላገጠማት ታስረዳለች።‹‹እኔ ዘንድ የለም ማለት ግን ሌላ ሰው ጋ የለም ማለት አይደለም፣ ልጄ ገና ሕፃን ሳለ አንዳንድ ጊዜ ቤት ሲያስቸግረኝ ይዤው ስወጣ ሰማይ ሰማይ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ጎን እያየ ስለሚሄድ ይህንን ያዩ የሰፈራችን አዛውንት ይሄ ሁኔታ የተለመደ እንዳልሆነና ጉዳት ሊያደርስበት ስለሚችል እንድጠነቀቅና ለሐኪም እንዳሳየው ይወተውቱኝ ነበር፣ እኔም ከዚያ ወዲህ ነው የልጄን ያልተለመደ ባህሪ ማጥናት የጀመርኩት›› በማለት ታብራራለች፡፡

ይሁንና ዘጠኝ ዓመቱ አካባቢ እንደተለመደው ልታዝናናው ከቤት ይዛው በወጣችበት አጋጣሚ እግሩን እያነሳ ሲጫወት ያዩት አንዲት እናት ጠጋ ብለው እንደዚህ ዓይነት ልጅ ከቤት እንደማይወጣ፣ የሰው ዓይን ጥሩ እንዳልሆነ፣ እንደ እዚህ ዓይነት ልጆች ለፈጣሪ ቅርብ ስለሆኑ ቤት መቀመጥ እንዳለባቸው በመግለፅ እንደመከሯትም ታስታውሳለች።ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች ያሏቸው ሌሎች እናቶችም እንደተረገሙ፣ በሰሩት ሐጥያት ፈጣሪ ተቆጥቶባቸው እንደሆነ በማህበረሰቡ እየተነገራቸው ኑራቸውን ጠልተው ራሳቸውን እስከማጥፋት የሚደርሱበት አጋጣሚ ስለመኖሩ መስማቷንም ታስረዳለች።

እሷ እንዳለችው፣ እንደዚህ ዓይነት ልጆች ባሉበት ቤተሰብ ትምህርት ቤት በማጣትና ማህበረሰቡ በሚያደርግባቸው ማግለል ምክንያት ብዙ ትዳር ይፈርሳል፣ ብዙ የተማሩና ትልቅ ቦታ መድረስ የሚችሉ ሰዎች ቤት ውስጥ ቀርተዋል።

ከዚህም አልፎ ሌሎች ልጆቿንም የምትጎዳበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ጠቅሳ፣ ትልቅ ቦታ የመድረስ ህልማቸው እንደሚጨናገፍ በተጨባጭ እንደሚታይ ታመለክታለች።በዚህ ምክንያት ልጆች ያለእድሜያቸው ጎዳና ላይ የሚወጡበት ሁኔታም ይፈጠራል ስትል ጠቅሳ፣ ‹‹ዛሬ እኔና ባለቤቴ ስላለን ልጆቻችንን ተንከባክበነን አሳድገናል፣ ነገ ባንኖር ግን የሀገር ሸክም ነው የሚሆኑት›› ስትል አስገንዝባለች።በድምሩ ከኦቲዝም ጋር አብረው የተወለዱ ልጆችንን የሚያስተናግድ ሥርዓትም ሆነ ተቋም ያለመኖሩ ለሀገር ትልቅ ኪሳራም ነው ባይ ነች።

እንደ ወይዘሮ ራሄል ገለፃ፣ ነህሚያ ኦቲዝም ሴንተር ከተመሠረተ ሰኔ ወር ላይ ዘጠኝ ዓመት ይሆነዋል።ድርጅቱን የመሠረተችበት ምክንያትም ለኦቲዝም ተጠቂዎች የሚሆን የትምህርት ተቋም በአቅራቢያዋ ያለመኖሩ ሲሆን፣ ህመሙ በቤቷ በመኖሩ እሷና ባለቤቷ እንደእነሱ የተቸገሩ ወላጆችን ያቅማቸውን ያህል ለማገዝ በማለም ነው።

በተለይም እናቶች ከተደበቁበት ወጥተው ልጆቻቸውን ሙሉ እምነት ይዘው የሚያስቀምጡበት ቦታ መፍጠርና የራሳቸውን ሥራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነው።ልጆችም ከታፈኑና ከተጨናነቀ ቤት ወጥተው ሰፊ ለምለም መስክ ባለበት ጊቢ ውስጥ የሚዝናኑበትና የሚቦርቁበትን ሥፍራ ለመፍጠርም ያለመ ነው።

ለዚህ ዓላማ መሳካት ያስችላት ዘንድም ወደ ቤተክርስቲያን በቀጥታ በመሄድ የሚያቋትን አገልጋዮችና ምዕመናን እንዲያግዟትና ድጋፍ እንዲያደርጉላት ተማፅነች።እነሱም አለሳፈሯትም፣ የአቅማቸውን ለገሷትና ቤቷን ተከራየች፣ አንዳንድ የሚያስፈልጋትን መሠረታዊ ቁሳቁስ አሟልታ ኦቲዝም ያለባቸውን ሕፃናት መንከባከብ ጀመረች።

‹‹ትልቁ ነገር ግን በማህረሰቡ ዘንድ ስለኦቲዝም ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ እድሉን ማግኘታችን ነው›› ስትል ገልጻ፣ የባልና ሚስቱን ጥረት ያየ አንድ ሰው ደግሞ የሚሰራው ፕሮጀክት ጊዜው ያለፈበት (ፌዛውት ያደረገበት) መሆኑን ጠቅሶ የቤቱን እቃ በሙሉ እንደሰጣቸው ትናገራለች።

‹‹ነህሚያ የእኔም የብዙዎች የፀሎት መልስ ነው፣ እግዚአብሔር ስለረዳን በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍቃድ አግኝተን ነው ተቋሙን ማስፋፋት የቻልነው›› የምትለው ወይዘሮ ራሄል፣ ተቋማቸው ልጆቹን ከተረከበ በኋላ የተለያዩ ደረጃዎች ያሏቸውን ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን በመስጠት ከማህበረሰቡ ጋር በቀላሉ መግባባት እንዲችሉ፣ ለመደበኛ ትምህርት ቤት የማብቃት ሥራ እንደሚሠራ ገልጻለች።የልጆቹ በተቋሙ ውስጥ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ እንዳሉበት የኦቲዝም መጠን የሚለያይ መሆኑን ገልፃ፣ በአሁኑ ወቅት ተቋማቸው 80 ተማሪዎች እንዳሉት ትጠቁማለች። በተጨማሪም 30 ከኦቲዝም ጋር የተወለዱ ተማሪዎችን አሰልጥኖ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት መላክ መቻሉን ትገልፃለች።

እንደ ወይዘሮ ራሄል ማብራሪያ ፣ የኦቲዝም ማዕከሉ ቋሚ የገቢ ምንጭ ባይኖረውም በየጊዜው የገቢ ማሰባሰቢያ መርሃ-ግብር ያዘጋጃል፣ ባንኮችን፣ ኢንሹራንሶችና አትራፊ ኩባንያዎች ድጋፍ እንዲያደርጉለትም ቅስቀሳ ያደርጋል።አሁን ላይ በተለይ መንግሥታዊ ተቋማት የማዕከሉን በጎ ሥራ በገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ጀምረዋል።ከእነዚህም መካከል የኢትዮጵያ ልማት ባንኩ ተጠቃሽ ነው።ባንኩ ከአራት ወር በፊት ሁለት ሚሊዮን ብር ድጋፍ ለማዕከሉ የሰጠ ሲሆን፣ ይህም ማዕከሉ ለጀመረው ሥራ መስፋፋትና መጠናከር ያግዛል፡፡

‹‹አሁን ላይ ማዕከላችን ያለበት ጊቢ ካሉት ተማሪዎች አንፃር ጠባብ የሚባል ነው፣ ከ53 በላይ ሠራተኞች ቢኖሩንም ሁሉንም ልጆች በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችል አቅም ስለሌለን በሳምንት ሁለት ጊዜ ከፍለን 40 ልጆችን በመጀመሪያዎቹ ሶስት ቀናት በመቀጠልም ባሉት ቀናት ቀሪዎቹን 40 ተማሪዎች እያሰለጠንን ነው ያለነው›› በማለት ታብራራለች።ባንኩ ማዕከሉ ያጋጠመውን ችግር በመረዳት ከሰሞኑ ደግሞ ተጨማሪ ሶስት ሚሊዮን ብር እንዳባረከተላቸው ነው የማዕከሉ ዳይሬክተር የጠቆመችው።ንግድ ባንክና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን የመሳሰሉ መንግሥታዊ ተቋማትም ከማዕከሉ ጎን በመቆም አለኝታ እንደሆናቸውም ጠቅሳለች፡፡

ወይዘሮ ራሔል እንደምትለው፣ መጀመሪያ ላይ የእናቶችን ድካምና እንግልት ለመቀነስ ማዕከሉን በየአካባቢው የማስፋፋት እቅድ ነበራት።ሆኖም ካለው ሀገራዊ ሁኔታ አንፃር ይህንን ማሳካት በቀላሉ የማይቻል መሆኑን በሂደት ተገነዘበች።በኋላም አስር ዓመት ላይ አዳሪ ትምህርት ቤት ለመክፈት አልማ መሥራቷን ቀጠለች።ይህ ትልሟ በተለይ በኩላሊት፣ በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ፣ በኮቪድ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት እጇ ላይ ያሉ በመሆናቸው ደረጃውን የጠበቀና በአግባቡ በሞግዚት ታግዘው እንዲያድጉ የሚያግዝ ነው።ግን ደግሞ ይህንንም ማሳካት የተራራ ያህል ከባድ ሆነባት፣ ይልቁንም አሁንም ድረስ የግለሰብ ቤት ተከራይታ ነው እየሰረች ያለችው።በመሆኑም ይህንን ችግሯን የተረዳ የመንግሥት አካል ቦታ ይሰጠኛል የሚል እምነት እንዳደረባትም ገልጻለች።

‹‹ይህ መሆን ከቻለ ብዙ ሕፃናትና እናቶቻቸውን እናሳርፋለን፣ በነገራችን ላይ ነህሚያ ለሕፃናቱ ብቻ ሳይሆን ለእናቶች የሥራ እድል ይፈጥራል፣ እናቶችን እናሰለጥናለን፣ እናማክራለን፣ በጣም የተጎዱና ራሳቸውን ለማጥፋት የሞከሩ እናቶች አሁን በማዕከሉ ያሉ በመሆኑ የእነሱንም ሕይወት የመታደግ ሥራ ይሠራሉ›› ስትል የወደፊት እቅዷን አጋርታናለች።

ይህ ብቻ ሳይሆን እንደሀገር በኦቲዝም ዙሪያ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ ይህንንም ችግር በመፍታት ረገድ ነህሚያ ወሳኝ ሚና ለመጫወት አስቧል።እነዚህ ሁሉ እቅዶቹን ማሳካት የሚችለው ግን አሁንም የመልካም ሰዎችና ተቋማት በጎ እጆች ሲዘረጉላቸው ብቻ እንደሆነ ነው ያስገነዘበችው።

በአሁኑ ወቅት ኦቲዝም ብዙ ቤት እየገባ ነው፣ በመሆኑም ልክ እንደእኔ ኦቲዝም ሩቅ አድርጋችሁ አታስቡት፣ መዘናጋትም የለብንም፣ የእኔ ልጅ ኦቲዝም እንዳለበት በታወቀበት ጊዜ ከ15 ሺ አንድ ልጅ ላይ ነው ይገኝ የነበረው።አሁን ላይ ግን ከ36 ልጅ በአንዱ ላይ እየተገኘ ነው።ይሄ አሃዝ አስደንጋጭ ነው።ስትል አስገንዝባለች።‹‹ ኦቲዝም በቀላሉ የምናየው አይደለም።በመሆኑም ሁሉም ሰው በቻለው መጠን ኦቲዝም ልጆችን መርዳት፣ በየቦታው ማዕከላት እንዲከፈትላቸው የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት፣ እንዲህ ዓይነት ልጅ ያላትን እናት በማግለልና ጫና በማሳደር ሌላ ሥራ ላለመሆን መጣር፣ ይልቁንም ጥንካሬዋን እየነገሩ ማበረታታት ይገባዋል ስትል ወይዘሮ ራሔል ለማህበረሰቡ መልእክቷን አስተላልፋለች፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ዓርብ ስፖርት



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ከፍተኛ ሊግ የተቀሳቀሱ አራት ክለቦች ተለይተዋል

**ዓለማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ የእግር ኳስ ውድድር በሀገሪቱ የሊግ እርከን ሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝና በርካታ ክለቦች የሚፋለሙበት ነው። በውድድሩ ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ክለቦች ወደ ከፍተኛ ሊግ እና ውጤት ያልቀናቸው ወደ ክልል ክለቦች ቻምፒዮና የሚወርዱበትም መድረክ ነው። ዘንድሮ በሁለት ምድቦችና በሁለት ዙሮች ሲካሄድ ቆይቶ ከትናንት በስቲያ ሲጠናቀቅ ወደ ከፍተኛ ሊግ ያደጉ አራቱም ክለቦች ተለይተው ታውቀዋል።

በህዳር ወር በሁለት ምድቦች ተካፍሎ በርካታ ክለቦችን በማፋለም የተጀመረው ጉዞ በ2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሊግ ውድድር የሚሳተፉ ክለቦች ሲለዩበት ከከፍተኛ ሊጉ የሚወርዱትን አምስት ክለቦች በመተካት በሁለተኛው የሀገሪቱ ሊግ የሚወዳደሩ ይሆናል። ለመጫወት የሚያስችላቸውን ውጤት ማስመዝገብ በመቻላቸው ሊያድጉ ችለዋል። የመጀመሪያው ዙር ምድብ የ"ሀ" በጅማ ከተማ እና የምድብ "ለ" ውድድሮች በሶዶ ከተማ ተካሂደው ከተጠናቀቁ በኋላ የውድድር ስፍራ ለውጥ በማድረግ መጋቢት 1/2016 ዓ.ም የምድብ "ሀ" ወድድሮች በሆሳዕና ከተማ የምድብ "ለ" ጨዋታዎች ደግሞ በአርባምንጭ ከተማ በመከናወን ከየምድቡ ሁለት ሁለት ክለቦችን በመለየት ነበር ወደ ከፍተኛ ሊግ ያደጉት ክለቦች የተለዩት።

ከምድብ "ሀ" ዱራሜ ከተማ እና አምቦ ከተማ፤ ከምድብ "ለ" ደግሞ ሱሉልታ ክፍለ ከተማ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ወደ 2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሊግ ማደጋቸውን ያረጋገጡ ክለቦች ሆነዋል።

ከአራቱ ክለቦች ቀድሞ ማደግ የቻለው ሱሉልታ ክፍለ ከተማ ሲሆን፤ የመጀመሪያውን ዙር 5ኛ ደረጃ በመያዝ ውድድሩን ቢያጠናቅቅም፤ በሁለተኛው ዙር አስደናቂ ጉዞን በማድረግና ከፍተኛ ነጥቦችን በመሰብሰብ ወደ ከፍተኛ ሊጉ ማደግ ችሏል። ሶስት ጨዋታዎች እየቀሩት ከ31 ጨዋታዎች 60 ነጥቦችን በመሰብሰብ ነባር የመጀመሪያው አዳጊ ክለብ መሆን የቻለው። በ31ኛው ሳምንት ከቡታጅራ ከተማ ጋር ባካሄደው ጨዋታ 3 ነጥብ ማሳካቱን ተከትሎ እና ሶስተኛ ደረጃ ላይ ከተቀመጠው አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በ10 ነጥቦች በመራቁ ወደ ከፍተኛ ሊግ ካደጉ ክለቦች መካከልም ሆኗል።

አምና በከፍተኛ ሊግ ሲወዳደር የነበረው አምቦ ከተማ ከአንድ ዓመት የከፍተኛ ሊግ ቆይታ በኋላ ሁለተኛው አዳጊ ክለብ በመሆን ወደ ነበረበት መመለስ ችሏል። ከ33 ጨዋታዎች በሰበሰባቸው 67 ነጥቦች ሶስተኛ ደረጃ ላይ የነበረውን ክለብ በአራት ነጥቦች በልጦ ነው ዳግም ከፍኛ ሊጉ ያደገው።

ዓመቱን በሙሉ የምድብ "ለ" ደረጃ ሰንጠረዥን በወጥነት እየመራ ማጠናቀቅ የቻለው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከበርካታ ዓመታት የአንደኛ ሊግ ቆይታ በኋላ ሶስተኛ ክለብ በመሆን ከፍተኛ ሊጉን ተቀላቅሏል። 33 ጨዋታዎችን በማድረግ 62 ነጥቦችን ሰብስቦ ሱሉልታን በመከተልም ነው ማደጉን ያረጋገጠው። 2008 ዓ.ም ላይ ወደ ከፍተኛ ሊግ ከወረደ ስምንት ዓመታት በኋላም ነው ተመልሶ ማደግ የቻለበትን ታሪክ ያስመዘገበው።

የመጨረሻው ዱራሜ ከተማ ሲሆን፤ እሱም በ2015 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ሊግ ወርዶ በዓመቱ ተመልሶ ማደጉን ያረጋገጠ ክለብ ሆኗል። በዚህም ካደረጋቸው 34 ጨዋታዎች 67 ነጥቦችን በመሰብሰብ ከምድቡ አምቦ ከተማን በመከተል ወደ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ሊግ ማደግ ችሏል።

የምድብ ሀ ጨዋታዎች ከትናንት በስቲያ የተጠናቀቁ ሲሆን፤ አምቦ ከተማ የውድድሩ አጠቃላይ አሸናፊ በመሆን የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችሏል። ዱራሜ ከተማ ሁለተኛ እና ቡራ ክፍለ ከተማ ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ሲያጠናቅቁ፤ የስፖርታዊ ጨዋነት ዋንጫውን ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወስዷል። በምድብ "ለ" ሱሉልታ ክፍለ ከተማ ውድድሩ አጠቃላይ አሸናፊና የዋንጫ ተሸላሚ ሲሆን፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና አቃቂ ቃሊቲ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ፈፅመዋል። ቡሌ ሆራ ደግሞ የስፖርታዊ ጨዋነት ዋንጫ አሸንፏል።

ከምድብ "ሀ" አራት ክለቦች ከምድብ "ለ" ደግሞ ሶስት ክለቦች በድምሩ ሰባት ክለቦች በተለያዩ ምክንያቶች ውድድራቸውን ያቋረጡ ሲሆን፤ ከየ ምድቡ ሁለት-ሁለት ክለቦች ወደ ክልል ክለቦች ቻምፒዮና መውረዳቸው ተረጋግጧል።




ሱሉልታ ከፍተኛ ሊጉን የተቀላቀለ የመጀመሪያው ክለብ ሲሆን ሌሎች 3 ክለቦችም ማደጋቸውን አረጋግጠዋል፤

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
Ministry of Labor and Skills
ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የኢንዱስትሪ ሰላም ለመፍጠር እያገዘ ያለው ምክክር

**ሰላማዊት ውቤ**

ሰላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነት ማስፈን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ወሳኝ ነው። ብሎም ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገትና ለጤናማ የሥራ ውድድር በእጅጉ አስፈላጊና አነቃቂም እንደሆነ በመስኩ ባለሙያዎች ሲነገርለት ይደመጣል። የኢንዱስትሪ ሰላም የአሰሪና ሠራተኛ ግንኑነት መልካም እንዲሆንም ሚናው የጎላ ነው።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ይሄን እውነታ መሰረት አድርጎ በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባት በትብብርና በምክክር መፍታት እንዲቻልና የኢንዱስትሪ ሰላም ይሰፍን ዘንድ እየሰራ ይገኛል። በተከታታይ የሚካሄድ የምክክር ስርዓቶች በመዘርጋት እንዲገነቡ እያደረገ ነው። በዚህ የምክክር ስርዓት ውስጥ ዋንኞቹ ተዋናዮች አሰሪና ሠራተኛ አደረጃጀቶች ናቸው።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በአሰሪና ሠራተኛ ዘርፍ የኢንዱስትሪ ግንኙነት ዴስክ ተወካይ ውብሸት ዘለለውም በምክክር መድረኩ የሠራተኛ አደረጃጀቶች፤ ዘጠኙ ፌዴሬሽኖች፤ የሰራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽኖች መሳተፋቸውን ያወሳሉ። በሂደቱም ከባለ ድርሻ አካላቶች ጋር የጋራ መግባባት መፍጠር መቻሉንና የጋራ አድርጎ ከመሄድ አንፃር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሻለ ውጤት ማምጣቱን ያነሳሉ። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ሆነ ሌሎች ባለድርሻ አካላት አስቻይ ሁኔታ የመፍጠር ስራ ይሰራሉ።

እንደ ተወካዩ ገለፃ የኢንዱስትሪ ሰላም ዓለም አቀፍ መርሆዎችን መሰረት ያደረገ ነው። ኢትዮጵያ የዓለም ሥራ ድርጅት አባል እንደመሆኗ የፈረመቻቸውን ዓለም



ውብሸት ዘለለው

አቀፍ መርሆዎችን፤ የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሰረት አድርጋ ትከውናለች። የሀገሪቱ የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅም፤የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣የወጡ መመሪያዎችም አለም አቀፍ ስምምነቶችን ተመርኩዘው ይተገበራሉ።

ለአብነት የጠቀሱት የአሠሪና ሠራተኛ ማህበራት ምዝገባ አንዱ ነው። በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ የሚመዘገቡት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ተቀማጭነታቸው ከአንድ ክልል በላይ ለሆኑ ድጋፍ እንደሚያደርግም ይጠቅሳሉ። የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወይም ግንኙነትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ስርዓቶችን መዘርጋት፤መቆጣጠር እና መተግበር በዴስኩ አማካኝነት እያከናወነ ከሚገኙት ተግባራት መካከል እንደሚጠቀሱም ነግረውናል። ሌሎች ተጨማሪ የኢንዱስትሪ ሰላም ሊያሰፍኑ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ እንደሚገኝም ያስረዳሉ።

የኢንዱስትሪ ሰላም ዋና መነሻው ማህበረሰብ ነው። የማህበረሰብ አካል ነው ብሎ መውሰድም ይቻላል የሚሉት የዴስክ ተወካይ ኃላፊው፤ ከማህበረሰቡ የሚቀዱት ግንዛቤዎች፤አመለካከቶችና ዕውቀቶች ኢንዱስትሪ ውስጥ ይገቡና የኢንዱስትሪው ባህል እየሆኑና እየዳበሩ ይሄዳሉም ብለዋል። ከዚህ በተቃራኒ ሊታረሙ የሚገባቸው ደግሞ ኢንዱስትሪ ውስጥ አብረን ይዘናቸው እንሄድና ለኢንዱስትሪው ሰላም ዕድገት ለምርታማነት እንቅፋት የሚሆኑበት የተለያዩ አጋጣሚዎች እንዳሉም ይናገራሉ።

በተለይ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አሁን ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራበት ያለው በአዲሱ የለውጥ እሳቤ ውስጥ አሰሪና ሠራተኛን ግንኙነት ምርትና ምርታማነትን መሰረት አድርጎ ከግንኙነት በላይ ማላቅ ስለመሆኑም ያነሳሉ። እንደ ሀገር ምርትና ምርታማነትን በተመለከተ ያለንበት እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ነው ያሉት ይሄንኑ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሻገር የሚተጋበት ሂደት ስለመኖሩም ያስረዳሉ። ተግባሩ አሰሪና ሠራተኛው በራሱ ዕውነቶች/ኩነቶች ላይ ተመስርቶ የምክክር ስርዓቱ የዳበረ እንዲሆን በማድረጉ ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚጨወትም ያብራራሉ።

በተለይ በሥራ ቦታዎች ላይ የሚደረጉ ምክክሮች ዋንኛ እና ዓይነተኛ የኢንዱስትሪ ሰላም ማስፈኛ መሣሪያዎች ናቸው። ለዚህም ሲባል የአሠሪና ሠራተኛ የጋራ እውነት ምንድነው የሚለው በሰፊው የሚቃኝበት ዓውድ መዘርጋቱን ተወካዩ ያስረዳሉ። ዓውዱ የአሰሪና ሠራተኛን ግንኙነት በመገንባት ሀገር አቀፍ ምርታማነትን ማሻሻል፣ማሳደግ፣ የግለሰቦች የማምረት አቅምንና ሥራቸውን ያልቃል፤ የማሻሻል አቅም መገንባት ያስችላል። ሃሳብን በነፃነት ማንሸራሸር ያስችላልና ከምርታማነት በኋላ ሁሉንም አሸናፊና ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ስለመሆኑም ያብራራሉ።

አቶ ውብሸት እንደሚሉኩት ጠንካራ የኢንዱስትሪ ማህበረሰብ መገንባት ላይ ትኩረት ተደርጎ በስፋት እየተሰራ ነው። በተለይም በቅርቡ በተጀመረው የለውጥ ሥራ በመጀመሪያው ክላስተር ከ352 ተቋማት የተውጣጡ አመቻቾችና አስተባባሪዎች ማሰልጠን መቻላቸውን በማሳያነት ይጠቅሳሉ። በተጨማሪም የአሰሪና ሠራተኛው ምክክር በተቋም ደረጃ እንዲካሄድ ሀሳቦች በነፃነት እንዲንሸራሸሩ ዓለም አቀፋዊ፣አህጉራዊ፣ተቋማዊና ግለሰባዊ እውነቶችን በአግባቡ እንዲፈትሹ ስለመደረጉም ያስረዳሉ። በክልልና በከተማ አስተዳደሮች ያሉ አስፈፃሚ አካላቶችን የዚሁ ስልጠና አካል መሆናቸውንና ምክክሩ በተከታታይ የሚካሄድበት ሁኔታ ስለመኖሩም ያብራራሉ።

የኢንዱስትሪ ሰላም የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመለከትና በጤናማ ግንኑነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሥራ ዕድል ፤የሥራ ቦታ መብት ፤ማህበራዊ ጥበቃ እና ምክክር አራቱን ምሶሶዎች መሰረት ያደረገ ነው።

በመሆኑም በኢንዱስትሪ ሰላም አለመኖር ምክንያት የሚከሰተውን ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ይቀንሳልና ሰላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ለመፍጠር በየደረጃው የሚገኙ ተቋማት ፤ሠራተኞች ፤አሰሪዎች በአሰሪና ሠራተኛ ዘንድ ግንዛቤ በመፍጠር የድርሻቸውን እንዲወጡ ያስችላል። የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ምክክሩ ላይ አጀንዳ መቅረጽና መስጠት ባይቻልም ግብረ ኃይል አቋቁሞ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ እየሰራ ይገኛል። ምክክሩና ትብብር ሥራው በሀገር ደረጃ ምክክር የሚደረግባቸውን ጉዳዮች ለይቶና አንጥሮ ለማውጣት ዕድል ፈጥሯል፤ በራስ አቅም ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመፍታትም እያስቻለ ይገኛል።